

# የኢትዮጵያ ሴቶች ሁኔታና ፍላጎቶቻቸውን ለመለየት የተካሄደ ጥናት

**አጭር ሪፖርት**

ጥቅምት 2017
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Women and Social Affairs

Funded by the European Union

NEWA

OXFAM

# የኢትዮጵያ ሴቶች
## *ሁኔታና ፍላጎቶቻቸውን*
## ለመለየት የተካሄደ ጥናት

## አጭር ሪፖርት

*ጥቅምት 2017*
*አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ*

**የፕሮጀክት ፋይናንስ ድጋፍ**
የአውሮፓ ህብረት (EU)

**የፕሮጀክት ፈጻሚና አጋሮች**
የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (ኢሰማቅ/NEWA) ከኦክስፋም ኢንተርናሽናልና በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር (MoWSA) የሚመራ ከፍተኛ አማካሪ ፓነል ጋር በመተባበር።

**ጥናቱን ያካሄዱና ሪፖርት አጠናቃሪዎች**
ዚያደ ሃይሉ፣ ጥላሁን ግርማ፣ ቅድስት ገብረስላሴ፣ ዳንኤል ንጋቱ፣ ትርሲት ሳህለድንግል

Photo credit: https://www.flickr.com/photos/rod_waddington

# ስለ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፤ ስለ ኢሰማቅና ኦክስፋም

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1263/2004 የተቋቋመ የፌዴራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ነው። ሚኒስቴሩ የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የከተማ ድሆች፣ አቅመ ደካሞች እና የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም አጠቃላይ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ ይሰራል። ለበለጠ መረጃ www.mowsa,gov.et ድረ-ገጽን ይመልከቱ።

የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት (ኢሰማቅ-NEWA) በ2003 እ.አ.አ. የተቋቋመች ለትርፍ የማትሰራ ተመሳሳይ ዓላማ ባነግቡ የሴቶች ማህበራትና ድርጅቶች የተመሰረተችና የሴቶችን ዕድገት ለማምጣት እንዲሁም ጠንካራ ትብብርና የጋራ ድምጽ ለመፍጠር፥ የሴቶችን ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ እና ህጋዊ መብቶች እንዲከበሩ ከሚሰሩት ብሄራዊ የሲቪል ማህበራት አንዷ ናት። ለበለጠ መረጃ www.newaethiopia.org ድረ-ገጽን ይመልከቱ።

በተመሳሳይ ከ1970ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ ኦክስፋም መሰረታዊ የድህነት ምክንያቶችን እና መገለሎችን ለመፍታት ዘላቂ መተዳደሪያ ዘይቤዎች፤ የውሃና የአከባቢ ንፅህና ፣ የግብርና፣ አየር ንብረት ምርምር፣ስርዓተ-ፆታ እና የሰብአዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ይገኛል። ለበለጠ መረጃ www.oxfam.org ድረ-ገጽን ይመልከቱ።

ይህንን ጥናት የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት (ኢሰማቅ-NEWA) ከኦክስፋም ኢንተርናሽናል እና ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ተግባራዊ አድርገዋልች። የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከፍተኛ የባለሙያዎች የአማካሪ ፓነልም የቴክኒክ ድጋፉና ሞያዊ ምክር ሰጥቷል።

# መቅድም

የኢትዮጵያ መንግሥት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈንና የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማጎልበት ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ እመርታ አሳይቷል። ይህም ሊሆን የቻለው ኢፍትሃዊ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን ለመቅረፍ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመተግበሩ ነው። አሁን በስራ ላይ ያሉት ፖሊሲዎች መንግስት ለስርዓተ-ጾታ እኩልነት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳዩ ናችው። እነዚህ ጥረቶች ቢኖሩም በተንሰራፉት አድሎዊ ማኅበራዊ ደንቦች፣ ልማዳዊ ድርጊቶች እና በአንዳንድ ክልሎች እየተከሰቱ ባሉ ግጭቶች የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ተግዳሮቶችን እየፈጠሩ ይገኛሉ። ሴቶች እና ሴት ልጆች የፆታዊ ጥቃት እና በሌሎች የጥቃት ዓይነቶች ሰለባዎች እየሆኑና በግጭት ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮችን እተጋፈጡ ይገኛሉ።

ከዚህ ቀደም የተደረጉ ጥናቶች ጠቃሚነታቸው እንደተጠበቀ ሁኖ የተበታተኑ፤ ያልተሟሉ እና ወቅታዊ ባለመሆናቸው የሴቶችን ሁኔታ በተለይም በቀውስ ጊዜ ውስጥ ያለውን ሁኔታ በተመለከተ የተሟላ ግንዛቤ አይሰጡም። የሴቶችን ህይወት የሚመለከት አንድ ወጥ ጥናት አለመኖሩ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት እና እና ውጤታማ የተግባር ስራ ለመስራት እንቅፋት ሆኗል። ይህንን የመረጃ ክፍተት በመገንዘብ ይህ የኢትዮጵያ ሴቶች የዳሰሳ ጥናት (National Women Survey) እና አሳታፊ የድርጊት ጥናት (Participatory Action Research) የተዋሀዱበት ጠቃሚ፣ ወጥ እና ወቅታዊ የሆነ የኢትዮጵያ ሴቶቸ ሁኔታና ፍላጎትን የለየ ሰፊና አርአያነት ያለው ጥናት ተሰርቷል። በአይነታዊ /qualitative/ እና በመጠናዊ / quantitative/ የመረጃ አሰባሰብ እና አተናተን ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። በዳሰሳ ጥናቱ (survey) በመላ ሀገሪቱ 36,367 ቤተሰብ (households) ለቃለ መጠይቁ ምላሽ በመስጠት ተሳትፈዋል፡ ፡ በተጨማሪም፣ ለአይነታዊ ጥናት በስምንት የሀገሪቱ ክልሎች በእያንዳንዳቸው 20 ሴቶች የተሳተፉበት ሦሥት ሦሥት የሴቶች ቡደን ውይይቶቸ /WGD/ ተደርጓል።

በዚህ ጥናት የተሰበሰበው ወቅታዊ መረጃ ለፖሊሲ አውጪዎች፣ ለሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ተሟጋቾች፣ ሚዲያዎች እና ተመራማሪዎች ጠቃሚ ግብአት ይሆናል የሚል ጽኑ እምነት አለ። ፖሊሲ አውጪዎቹ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የልማት አጋርና ለጋሽ ድርጅቶች (donors and development partners) ደግሞ ሃገራዊ ፕሮግራሞቻቸውን፣ የሴቶችን ፍላጎቶችና ጥያቄዎችን በተሻለ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት ግብአት ያገኙበታል። የስርዓተ-ፆታ እኩልነት ተሟጋቾችም መረጃውን በመጠቀም ግንዛቤን ለማሳደግ እና አዎንታዊ የፖሊሲ ለውጦችን ለማቀንቀን ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የመገናኛ ብዙሃንም ቁልፍ የስር-ዓተ ጾታ ልማት ጉዳዮችን በማጉላት የህብረተሰባችንን ግንዛቤ ማጎልበት እና ተጠያቂነትን መጨመር ይችላሉ። ምሁራን ደግሞ የላቀ የስታቲስቲክስ ስልትን በመጠቀም ይህንን የተሰራውን ስራ እንደመነሻ በመውሰድ ሌላ ጨምረው የላቀ ስራ ለመስራት ይችላሉ።

ይህ የጥናት ሪፖርት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የአውሮፓ ህብረት፣ ኦክስፋም እና ኢሴማቅ የኢትዮጵያ ሴቶችን የተለያዩ ተግዳሮቶች ለመፍታትና ፍላጎታቸውን ለመለየትና ለመመለስ ያላቸውን ቁርጠኝነት አጉልቶ ያሳያል። ጥናቱን ለማካሄድ ጥቅም ላይ የዋለው ሃብት እነዚህ ተቋማት የኢትዮጵያ ሴቶችን የወደፊት ህይወት የበለጠ ፍትሃዊ ለማድርግ ያላቸው የጋራ ራዕይ አንዱ ማሳያ ነው።

**የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅትና ኦክስፋም ኢንተርናሽናል**

# እውቅና

በኢትዮጵያ የሴቶች ሁኔታ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች (EWSP) ላይ የተደረገው ይህ ጥናት ሊሳካ የቻለው በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ባደረጉት አስተዋፅኦ ነው። የአውሮፓ ህብረት (EU) የገንዘብ ድጋፍ ስላደረገ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን። የኢትዮጵያዊያን ሴቶችን ለማብቃት እና የፆታ እኩልነትን ለማጎልበት ያላቸው ቁርጠኝነት በዋጋ የማይተመን እና የሚደነቅ ነው።

በሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር (MoWSA) የሚመራው አማካሪ ፓናል ፕሮጀክቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ላበረከተው የቴክኒክ ድጋፍ፡ ምክርና ቁርጠኝነት ላቀ ያለ ምሰጋና እናቀርባለን። የክልሎች፣ የከተሞችና የወረዳ  የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች እና ጽ/ቤቶች ላደረጉልን ድጋፍ እናመስግናን። የሴቶች መብት ድርጅቶች፣ ማህበራት እና መዋቅሮቻቸው ድጋፍ አንዲሁም በእነዚህ መዋቅሮች ውስጥም ሆነ ውጪ ያሉት ሴቶች በአሳታፊ ተግባራዊ ጥናት (PAR) ላይ የነበራቸው ተሳትፎ ጥናቱን ውጤታማ አድርጎታል።

ጥናቱን ላጠኑና ሪፖርቱን ላደራጁ ዚያድ ኃይሉ፣ ጥላሁን ግርማ፣ ቅድስት ገብረሥላሴ፣ ዳንኤል ንጋቱ እና ትርሲት ሳህለድንግል፤ ለዳታ ማናጀር እና ፕሮግራመር ግሩም ጌታቸው እና የጥራት ቁጥጥር ኦፊሰር አማኑኤል ኪሮስ እንዲሁም የዳሰሳ ጥናት አመራር፡ የኢኮን አመራሮች  (ECON M. Consultants) እና የአባመላ ቢዝነስ አማካሪዎች  (ABAMELA Business Consulting)  ያሳዩት የሰው ሃይልና ሎጂስቲክስን የማስተባበር ብቃት እና አርአያነት  ምስጋና ያስቸራቸዋል።  እንዲሁም በስምንት ክልሎች የአሳታፊ ተግባራዊ ጥናት (PAR) ሲካሄድ እና ያስተባበሩ የጥራት ምርምር ሱፐርቫይዘሮችና አስተባባሪዎች  ልዩ እውቅና ለመስጠት እንፈልጋለን። በመጨረሻም፣ ጊዜያቸውን፣ ልምዳቸውን እና ግንዛቤያቸውን ለለገሱን የጥናት ተሳታፊዎች ልባዊ ምስጋና እናቀርባለን።

ከላይ የተገለጹት ግለሰቦች እና ድርጅቶች የእያንዳንዳቸው ትብብር እና ቁርጠኝነት ባይኖር ኖሮ ይህ ጥናት ሊሳካ አይችልም ነበር። ይህ የአጋሮች ትብብር የኢትዮጵያ ሴቶችን ችግሮች ለመፍታት የማይተካ  ሚና አለው።

**የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅትና ኦክስፋም ኢንተርናሽናል**

# ACRONYMS AND ABBREVIATIONS

| | |
|---|---|
| AIDS | Acquired Immunodeficiency Syndrome |
| BGRS | Benishangul Gumuz Regional State |
| CBO | Community-Based Organizations |
| CSA | Central Statistical Agency |
| DHS | Demographic and Health Survey |
| DG | Discussion Group |
| EA | Enumeration Area |
| ESS | Ethiopian Statistics Service |
| EU | European Union |
| FCV | Fragility, Conflict, and Violence |
| GBV | Gender-Based Violence |
| GGGI | Global Gender Gap Index |
| HIV | Human Immunodeficiency Virus |
| ICT | Information and Communications Technology |
| IDRC | International Development Research Centre |
| IFPRI | International Food Policy Research Institute |
| IUD | Intrauterine Device |
| LMS | Labor Force and Migration Survey |
| MSE | Micro and Small Enterprises |
| NEWA | Network of Ethiopian Women Associations |
| NGO | Non-Governmental Organization |
| OXFAM | Oxford Committee for Famine Relief |
| PAR | Participatory Action Research |
| PSNP | Productive Safety Net Program |
| PwD | Persons with Disability |
| SEW | Survey of Ethiopian Women |
| SHG | Self-Help Group |
| SPSS | Statistical Package for the Social Sciences |
| STATA | Statistical Software for Data Science |
| TV | Television |
| TVET | Technical and Vocational Education and Training |
| WEAI | Women's Empowerment in Agriculture Index |
| WGD | Women Group Discussion |
| WG | Women Group |





# ማውጫ

## የኢትዮጵያ ሴቶች
### *ሁኔታና ፍላጎቶቻቸውን*
### ለመለየት የተካሄደ ጥናት

**መቅድም** ........ i

**እውቅና** ........ ii

**1. የጥናቱ ዳራ** ........ 1
1.1 መግቢያ ........ 1
1.1.1 አጠቃላይ እይታ ........ 5
1.1.2 የጥናቱ ዓላማዎች ........ 6
1.2 የጥናቱ ስነ-ዘዴ ........ 6
1.2.1 የዳሰሳ ጥናት ዘዴ ........ 6
1.2.2 የአይነታዊ ጥናት ዘዴ ........ 7
1.2.3 የመጠናዊ እና አሀዛዊ ዘዴዎች ቅይጥ ........ 7
1.2.4 የጥናቱ ተግዳሮቶች እና ውስንነቶች ........ 7
1.2.5 የትንተና ማዕቀፍ ........ 8

**2. ጥናቱ የተዳሰሱ ጭብጦችና የተገኙ ውጤቶች** ........ 10
2.1 ቁልፍ ጭብጦች በሴቶች ህይወት ........ 10
2.1.1 የሴቶች የኢኮኖሚ ሁኔታ ........ 10
2.1.2 የጤና ሁኔታ ........ 11
2.1.3 የትምህርት ተደራሽነት ........ 12
2.2 ተግዳሮቶች እና ተግዳሮቶችን ስለመቋቋም ........ 12
2.2.1 ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ........ 13
2.2.2 የስልቦናዊ ደህንነት እና ጉዳቶችን መቋቋም ........ 13
2.2.3 የፍትህ ተደራሽነት ........ 14
2.3 ፍላጎት እና ውክልና ........ 14
2.3.1 ሴቶች ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች እና ምኞቶች ........ 14
2.3.2 ፖለቲካዊ እና ህዝባዊ ተሳትፎ ........ 14
2.3.3 የሰላም እና የደህንነት ሁኔታ ........ 15

**3. መደምደሚያ እና ምክረ ሃሳቦች** ........ 16
3.1መደምደሚያ ........ 16
3.2ምክረ ሃሳቦች ........ 19

**ዋቢዎች** ........ 25



# የኢትዮጵያ ሴቶች ሁኔታና ፍላጎቶቻቸውን
ለመለየት የተካሄደ ጥናት

# 1 የጥናቱ ዳራ

## 1.1 መግቢያ

### 1.1.1 አጠቃላይ እይታ

የኢትዮጵያ መንግሥት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እና የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ቁርጠኛ ሲሆን እነዚህን ግቦች የሚያግዙ በርካታ ተቋማዊ እና የፖሊሲ እርምጃዎችንም ወስዷል። የሴቶችን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ማረጋገጥ እና ሴቶችን ማብቃት (GEWE) እንደ ሀገር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እና የፖሊሲ፣ የህግ እና ተቋማዊ ማዕቀፎችም ማዕከል ሁኗል። የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ለሴቶች የሚጠቅሙ ፖሊሲዎች፣ ህጎች እና ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ሆነዋል። ሥርዓተ-ፆታ በዋና ዋና ሀገራዊ እና ዘርፍ-ተኮር (sectoral) የልማት ዕቅዶች ማለትም እንደ ጤና፣ ትምህርት፣ ኢንዱስትሪ እና የመሳሰሉት ውስጥ ተካቷል። በተጨማሪም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ጉዳዮችን ለማካተት፣ ለማስተባበር እና ለመቆጣጠር ተቋማዊ አደረጃጀቶች ተፈጥሯል። ምንም እንኳን  እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ቢደረጉም የተለያዩ ወጎች እና ልማዶች እንዲሁም በአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋሉ የተራዘሙ ግጭቶች እስካሁን የተደረጉትን ጥረቶች የሚያሳንሱ ሁነዋል።በዚህም የተነሳ ሴቶች ጾታዊ ጥቃቶች እና የተለያዩ የመብት ጥሰቶችን ጫና እየተሸከሙ ይገኛሉ።

ከዚህ ቀደም በተያያዥ ጉዳዮች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ጠቃሚ ቢሆኑም ውስንነት አለባቸው፡፡ መረጃዎቹ ተበታትነው የሚገኙ እና በአንድ የስርዓተ-ጾታ ጉዳይ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ እንዲሁም በተወሰኑ የአገራችን ክፍሎችን ብቻ የሚሸፍኑ ናቸው። ለምሳሌ ከአገር አቀፍ ዳሰሳ ጥናት አልፎ ዘን ድረስ የሚሸፍኑ ዝርዝር ጥናቶች የሉም። ይህም ለሴቶች ችግር የተሟላ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ መፍትሄ የመስጠት ጥረት እንቅፋት ሁኖ ቆይቷል። ስለሆነም ይህንን ወቅቱን የጠበቀ እና የተሟላ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሁኗል።

ይህ የኢትዮጵያ ሴቶች ሁኔታ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ጥናት ሪፖርት (A Study on Ethiopian Women’s Status and Priotiries) እንደ አንድ አዲስ ምዕራፍ ከፋች የሚታይ እና ፋይዳ ያለው ነው። ከላይ እንደተገለጸው አሁን ላይ ካሉን የተበታተኑ፣ ያልተሟሉ እና ጊዚያቸው ካለፈባቸው የጥናት ውጤቶች ባሻገር ይህ ጥናት የሴቶችን ወቅታዊ ሁኔታ እና ፍጎቶችን ከብዙ ማሳያዎች አንጻር አይቶ፣ መጠናዊ እና አይነታዊ የጥናት ዘዴዎችን ተጠቅሞ የተሟላ እና ወቅታዊ መረጃዎችን አበርክቷል።  ይህ ትልቅ ጥናት በመላ ሀገሪቱ ከሚገኙ 36,367 ቤተሰብ ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና በ8 ክልሎች የሚገኙ 440 ሴቶችን በቡድን ውይይት በማሳተፍ እስካሁን ከተደረጉት ጥናቶች ሁሉ እጅግ በጣም ሰፊ እና ሁሉን አቀፍ ነው።

በዚህ ጥናት የሚገኘው አዲስ መረጃ ለፖሊሲ አውጪዎች፣ ለሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ተሟጋቾች፣ ለሚዲያዎች እና ተመራማሪዎች እንዲሁም ለሌሎች ብዙ ባለድርሻ አካላት እንደ ግብአት ሆኖ ያገለግላል። ፖሊሲ አውጪዎች ግኝቶቹን በመጠቀም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈን እና ሴቶችን ለማብቃት ለሚሰሩ ስራዎች  በግብዓትነት መጠቀም ይችላሉ። የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ተሟጋቾች ደግሞ የህበረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ፣ የፖሊሲ ለውጦችን ለማቀንቀን እና የህብረተሰብ ለውጥን ለማምጣት ለሚያደርጉት ጥረት ጥናቱ ጠቃሚ ግብዓት ይሆናቸዋል።  የሚዲያ ባለሞያዎች መረጃውን በመጠቀም ቁልፍ ጉዳዮችን ለማጉላት እና የህዝብ ውይይትን ለማዳበር ግንዛቤን እና ተጠያቂነትን ለመጨመር በሚያደርጉት ጥረት ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ምሁራን ደግሞ ከፍተኛ ደረጃ አህዛዊ ዘዴዎችን (statistical methods) በመጠቀም አዲስ  እውቀት ሊያክሉበት ይችላሉ።

### 1.1.2 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሴቶችን ደረጃ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮችን በተመለከተ የበተለያዩ ዘርፎች የተሟላ እና ወቅታዊ ማስረጃዎችን ማመንጨት ነው። እነዚም ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው፡- ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ጾታዊ ጥቃቶች፣ ስነ-ልቦናዊ ጤንነት፣ ፖለቲካዊ ተሳትፎ እና ህዝባዊ ሁኔታዎች፣ ሰላም እና ደህንነት እና የፍትህ ተደራሽነት ናቸው።፡- መጠናዊ ጥናቱ (quantitave study) የተካሄደው በ12 ክልሎች እና 2 ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሚገኙ በ119 ዞኖች/ከተሞች/ንዑሳን ከተሞች ከሚገኙ አባወራዎች/እማወራዎች ነው። አይነታዊ ጥናት (qualitative study) ደግሞ በ8 ክልሎች ከሚገኙ ሴቶች ጋር በአሳታፊ ተግባራዊ ጥናት (PAR) ዘዴን የቡድን ውይይት ተጠቅሟል።

### 1.1.3 የሪፖርቱ አደረጃጀት

ይህ ሪፖርት የኢትዮጵያን ሴቶች አኗኗር፤ የስነ ህዝብ አወቃቀር፤ የኢኮኖሚ፤ የጤና፤ የትምህርትና የመቋቋም አቅም ሁኔታዎችንና አመላካቾችን መሠረት በማድረግ የጥናቱን አጠቃላይ ዕይታ ያሳያል። እንዲሁም ፆታ ተኮር ጥቃቶች፤ የሴቶችን ሥነ-አእምሯዊ ደህንነትና የፍትህ ተደራሽነት ያሉበትን ደረጃ ያብራራል። ጥናቱ በተጨማሪም የሴቶችን ምኞቶችንና ለራሳቸው ድምፅና ወኪል ስለመሆን፤ ገቢያቸው፤ ድህንነታቸው፤ የፖለቲካ ተሳትፏቸው ምን መምሰል እንደሚፈልጉና እንዳለበት ይዳስሳል። ጥናቱ በመጨረሻም ለፖሊሲና ለፕሮግራም ግብአት ማጠቃለያ ሃሳብና ምክረ-ሃሳቦችን ያመላክታል።

## 1.2 የጥናቱ ስነ-ዘዴ

### 1.2.1 የዳሰሳ ጥናት ዘዴ (survey method)

በከተማ እና በገጠር ኢትዮጵያ ውስጥ እድሜያቸው 15 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ቤተሰቦችን የሚሸፍን አጠቃላይ የናሙና ዲዛይን ተሰርቷል። እ.ኤ.አ በ2018/2019 በኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ የተዘጋጀውን የናሙና ፍሬም (sampling frame) መሰረት በማድረግ ከ1,211 የቆጠራ አካባቢዎች (enumeration areas) የተውጣጡ 36,367 አባወራዎች/እማወራዎች ወካይ ናሙና ሁነው ተመርጠዋል። ፍሬሙ ባለ ሶስት እርከን የክላስተር ናሙና (cluster sampling) ንድፍ ዘዴን ተጠቅሞ 147,602 የቆጠራ አካባቢዎች እና በስሩ የሚገኙ አባወራ/እማወራዎችን ብዛት እና የመገኛ ቦታዎችን ለይቷል።

የዳሰሳ ጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ቅልጥፍና እና ጥራት እንዲኖረዉ ኮቦቱልቦክስ (kobotoolbox) ጥቅም ላይ ውሏል። መጠይቁ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን፣ ስነ-ጾታን ፣ ስነ ልቦናዊ ጉዳዮችን፣ ፍትህ ማግኘት፣ የሴቶች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች፣ የፖለቲካ ተሳትፎ እና ሰላም እና ደህንነትን ጨምሮ ሰባት መሪ ሃሳቦችን ያቀፈ ሲሆን መረጃው ዕድሜያቸው 15 እና ከዚያ በላይ ከሆኑ ምላሽ ሰጪዎች ገጽ-ለገጽ የተሰበሰበ ነው። የመስክ ስራው 160 መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 30 ሱፐርቫይዘሮች እና 5 አስተባባሪዎችን ያቀፈ ሲሆን እነዚህ ሰራተኞች መስክ ከመውጣታቸው በፊት ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷቸዋል።

የመረጃ አሰባሰብ ሂደትን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር ማይክሮ-ሶፍት ዳሽቦርድ ጥቅም ላይ ውሏል። ከመስክ የተገኘውን መረጃ ለማጽዳት እና ለመተንተን ኤስፒኤስኤስን፣ ስታታ እና ኤክሴል ጥቅም ላይ ውለዋል። ውጤቱም በስታቲስቲካዊ እና ማጠቃለያ ሠንጠረዦች፣ ግራፎችን እና ቻርቶችን አማካኝነት ቀርቧል። የአይነታዊ ጥናት ውጤቶች ደግሞ በጭብጣዊ ትንተና ዘዴ (thematic analysis) ቀርቧል።





የዳሰሳ ጥናት

36,330
አባወራዎች/እማወራዎች

1,211
የቆጠራ አካባቢዎች

15+
ዓመት በላይ የሆኑ ምላሽ ሰጪዎች

160
መረጃ ሰብሳቢዎች

30
ሱፐርቫይዘሮች


5
አስተባባሪዎች

### 1.2.2 የአይነታዊ ጥናት ዘዴ

ይህ የአሳታፊ የድርጊት ጥናት ዘዴ (Participatory action research -PAR) እ.ኤ.አ መስከረም 20 ቀን 2023 እስከ ታኅሣሥ 31 ቀን 2023 ድረስ በስምንት ክልሎች የተካሄደ ነው። ለዚህም ስራ ያመች ዘንድ የክልል ማዕከላትን ያቀፉ መሪ የምርምር ተቆጣጣሪዎች፣ የፕሮጀክት ኦፊሰሮች እና የሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅት ተወካዮች (WROs) የተሳተፉባቸው ማዕከለት ተቋቁመው ነበር። አሳታፊ የድርጊት ጥናት የተካሄደባቸው ቦታዎች (ክልሎች እና በየክልሎቹ የሚገኙ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች) የሚከተሉት ናቸው።

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፡- ሦስት ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች
- የአማራ ክልል - ባህር ዳር ከተማ
- የኦሮሚያ ክልል - መቱ (ኢሉ አባ ቦራ ዞን መቱ ወረዳ እና በስሩ የሚገኙ ቀበሌዎች)
- ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል - አሶሳ - ወረዳዎች አና ቀበሌዎች
- ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል - ጋሞ ዞን አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳዎች/ቀበሌዎች
- የትግራይ ክልል - መቀሌ፣ ሀውዜን እና ሃገረሰላም ወረዳዎች
- የአፋር ክልል - ዞን አንድ፡ ሰማራ፡ ሎጊያ፡ ዱብቲ
- የሰማሌ ክልል፡ ፋፋን ዞን (ባቢሊ፣ አውባሬ እና ቱሌ ጉሌድ ወረዳዎች)።

### የአሳታፊ የድርጊት ጥናት ቦታዎች



ከአማራ ክልል በስተቀር በእያንዳንዱ ክልል ሶስት የሴቶች ቡድኖች ተቋቁመው በድምሩ 22 ሴት ቡድኖች የቡድን ውይይት አድርገዋል። እያንዳንዱ የሴቶች ቡድን 20 ሴት አባላትን ያቀፈ ሲሆን በአጠቃላይ በእያንዳንዱ ክልል 60 አባላት አሉት። ስለዚህ በየክልሉ ሶስት ቡድን እና 60 ሴቶችን በማሳተፍ በድምሩ 440 ሴቶች በስምንቱ ክልሎች በቡድን ውይይቱ ተሳትፈዋል። በተጨማሪም የቡድን ውይይት መሪዎች፡ አስተባበሪዎች ተቆጣጣሪዎች በውይይት መመሪያዎች እና መሳሪያዎች የተቃኙ በምርምር ሂደቱ እና በሚጫወቱት ሚና ላይ ስልጠና የሚሰጥ የአምስት ቀናት አውደ ጥናት ተዘጋጅቶ ነበር።

## 1.2.3 የመጠናዊ እና አህዛዊ ዘዴዎች ቅይጥ

ይህ ሪፖርት ከላይ ከተጠቀሱት ሁለቱ የጥናት ዘዴዎች (መጠናዊ እና አይነታዊ) የተገኙ ውጤቶች ድምር ነው። ይህ ቅይጥ ዘዴ ሁለቱም የተለያዩ ጠንካራ ጎኖች ያለቸው ስለሆነ ሁለቱንም መጠቀም አንዱን ዘዴ ከመጠቀም ይልቅ የሚበልጥ ጥንካሬ አለው።

## 1.2.4 የጥናቱ ተግዳሮቶች እና ውስንነቶች

ይህ ጥናት የተካሄደው በአንዳንድ ክልሎች የተፈጠረው ግጭት በቀጠለበት ወቅት ነው። ይህም ለመረጃ አሰብሰብ ውስብስብ ሁኔታን ፈጥሯል። በተጨማሪም መረጃ የሚሰበሰብባቸው ቦታዎች የመልከዓ-ምድራዊ እና የሎጂስቲክስ ተግዳሮቶች ያሉባቸው ነበሩ። ለምሳሌ፣ በሶማሌ ክልል የዝናብ ወቅት ስለነበረ የመስክ ሰረተኞቹ እንደልብ ለመንቀሳቀስ ተቸግረው ነበር። በተጨማሪም በአማራ ክልል የነበረው የኢንተርኔት አገልግሎት ውስንነት መረጃ ሰብሳቢዎች መረጃን ለማጋራት ወደ ዋና ዋና ከተሞች እንዲመላለሱ አስገድዷል። ይህም የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ ላይ መዘግየትን ፈጠሯል፡፡ ሩቅ እና ይበልጥ ገጠራማ በሆኑ አካባቢዎች በቂ መረጃ ሰብሳቢ ሴቶችን ለመቅጠር የማያቋርጥ ጥረትን የሚጠይቅ ነበር። በአማራ ክልል የነበረው አስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ በእንቅስቃሴ እና በማህበራዊ ስብሰባዎች ላይ ገደቦች ጥሎ ስለነበር እንደልብ ከመረጃ ሰጭዎች ጋር ለመነጋገር አስቸጋሪ ነበር። ከላይ እንደተገለጸው የአሳታፊ የድርጊት ጥናት ዘዴ (PAR) ደግሞ የቡድን ውይይትን የሚጠይቅ ነበር። ታዲያ ለአማራ ክልል የተመደበው ውይይት ባህርዳር ላይ የተደረገ ሲሆን 20 ሴት ተወያዮች ጋር ብቻ የተደረገ ነበር።

እነዚህን ተግዳሮቶች ለመወጣት የመስክ ሰራተኞቹ ልምድ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። እነዚህ የመስክ ሰራተኞች ከዚህ ቀደም ከኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ጋር በመተባበር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መረጃ የመሰብሰብ ልምድ፣ ብልሃትና ቁርጠኝነት ያዳበሩ ናቸው። በተጨማሪም ግጭቱ የበረታባቸውን ቦታዎች ከጥናቱ ናሙና ውጭ እንዲሆኑ የማድረግ ስለታዊ ውሳኔ ተወስኗል። ይህም የመስክ ሰራተኞች ላይ ሊድረስ የሚችለውን አደጋ አስወግዷል። በተጨማሪም በእነዚህ ቦታዎች ላይ ተሳክቶ መረጃው ቢሰበሰብ እንኳ መረጃ ሰጭዎቹ በወቅቱ በነበረው ግጭት ላይ ትኩረት ስለሚያደረጉ የመረጃው ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል (ለምሳሌ በግጭት ወቅት የተፈጠሩትን ክስተቶች ብቻ የያዘ ጥናት ይሆናል)። ይህ ሲባል እነዚህ በከፋ ግጭት ውስጥ ያሉ ቦታዎች ሙሉ በሙሉ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም ማለት አይደለም። በምትኩ፣ አይነታዊ የጥናት ዘዴን በመጠቀም ቁልፍ ጉዳዮችን ለመዳሰስ ተችሏል።

በዚህ መሰረት የሚከተሉት ዞኖች ከዳሰሳ ጥናቱ ውጭ ሁነዋል። እነዚህም፡ በአማራ ሁለት ዞኖች (ደቡብ ጎንደር እና ምስራቅ ጎጃም)፣ በትግራይ ሁለት ዞኖች (ምዕራብ ትግራይ እና ደቡብ ትግራይ)፣ በኦሮሚያ አራት ዞኖች (ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ እና ምስራቅ ወለጋ) ናቸው። በምትካቸው ሌሎች ዞኖች በሳይንሳዊ መንገድ ተመርጠው ተተክተዋል። ቀድሞውንም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመቋቋም የአጥኚ ቡድኑ የመጠባበቂያ እቅድ (contingency plan) አዘጋጅቶ ነበር።

ምንም እንኳን ከላይ በተጠቀሱ ዘዴዎች ተግዳሮቶችን ለመፍታት እና ለመቋቅም ጥረት የተደረገ ቢሆንም ይህ ማለት ግን ጥናቱ ምንም አይነት ውስንነት የለበትም ማለት አይደለም። ለምሳሌ ባላው የግጭት ነባረዊ ሁኔታ ምክንያትም ይሁን በሌላ የመላሾቹ አመለካከት ሳቢያ በስነ-ልቦናዊ መለኪያዎች ላይ ሚዛናዊነት የሚጎድለው መልስ መሰጠቱ አይቀርም፡፡ ይህም የአንዳንድ መለኪያዎች ውጤት ተጋኖ እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል። ይህ የትኛውም ጥናት ላይ የሚንጸባረቅ ባህሪ ሲሆን ይልቁንም ከዚህ ጥናት የሚመነጩ ሌሎች ጉዳዮች የጥናቱን ውጤት ውስን እንዲሆን ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የጥናቱ ተሳታፊዎች ምላሽ ሲሰጡ ለሌሎች ጥሩ ለመምሰል እውነተኛ አስተያየታቸውን ሊደብቁ ይችላሉ፤ ስለዚህ በተለይም የዳሰሳ ጥናቱ ውጤቶች በጥንቃቄ መተርጎም እና አውዱን ግምት ውስጥ ማስገባት ነበረባቸው። ይህ ጥናት መጠናዊ ውጤቶችን ለመግለጽ የተጠቀመው መደበኛ ሪፖረት ማቅረቢያ መንገዶችን (standard reporting methods) ሲሆን ይህም ማለት ውጤቱን በፐርሰንት ማቅረብ ነው:: ፍለጎት ያላቸው አካላት የተሰበሰበውን ጥሬ መረጃ በመጠቀም ሌሎች የላቁ አህዛዊ የውጤት አቀራረብ እና አተናተን ዘዴዎችን በመጠቀም ሪፖርቱን ማዳበር ይችላሉ ፤ ለዚህ ሪፖርት አላማ ግን አሁን ያለው አቀራረብ በቂ ነው።

## 1.2.5 የትንተና ማዕቀፍ

ሴቶችን የማጎልበት ማዕቀፍ (Women Empowerment Framework - WEF) ሴቶችን ለማብቃት የሚያስችሉ የተለያዩ ዘርፎችን ለመገምገም እና ለማስተዋወቅ የተነደፈ ሁሉን አቀፍ የፅንሰ-ሃሳብ ማዕቀፍ ነው። በመጀመሪያ እንደ ካቢር (1999)፣ ራውላንድስ (2016) እና ሌሎችም በስርዓተ-ፆታ እና በልማት ዙርያ በሚያጠነጥኑ ምሁራን የተዘጋጀው ማዕቀፉ ሴቶችን ለማብቃት አስተዋጽኦ የሚያደርጉትንም ሆነ እንቅፋት የሚሆኑትን ጉዳዮች ለመረዳት ዘርፈ ብዙ አቀራረብን ይሰጣል። ይህ ጥናትም መሰረት ያደረገው ይህንን ማዕቀፍ ነው።

ሴቶችን ማጎልበት ማዕቀፍ (WEF) በርካታ ወሳኝ አካላትን ያጠቃልላል። የኢኮኖሚ ዘርፉ የፋይናንስ ሀብቶች ለሴቶች ስላለው ተደራሽነት እና ቁጥጥር፣ በስራ ገበያ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ እና በኢኮኖሚያዊ የውሳኔ ሰጪነት ስልጣን ላይ ያተኩራል። በትምህርት ሴቶችን የማብቃት ዘርፍ ደግሞ የሴቶችን የትምህርት ተደራሽነት፣ የትምህርት ደረጃዎችን ፣ የማንበብ እና መጻፍ ክህሎቶችን፣ እና የዕድሜ ልክ ትምህርት (lifelong learning) እና ክህሎቶች ዙርያ ያጠነጥናል። የጤና ዘርፍ ደግሞ ለሴቶች የሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ተደራሽነት፣ የስነ ተዋልዶ ጤናና መብቶችን፣ የአእምሮ ጤና ድጋፍን እና አጠቃላይ ደህንነትን ይመለከታል።

በተጨማሪም የስነ-ልቦና ዘርፍ ሴቶች ስለራሳቸው ስለሚኖራቸው አዎንታዊ ግምት፣ በራስ መተማመን፣ ራስን በራስ የማስተዳደር እና ከስነ-ልቦና ጥቃት ወይም ከማስገደድ ነጻ መሆንንም የሚመለከት ነው። የፖለቲካ እና የሲቪክ መብቶች የማጎልበት ዘርፍ ደግሞ ሴቶች በፖለቲካ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ፤ በውሳኔ ሰጪ አካላት ውስጥ ስለሚኖራቸው ውክልና እና በሲቪክ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ስለሚያደርጉት ተሳትፎ ይመለከታል። ማህበራዊ እና ባህላዊ ማጎልበት ደግሞ የስርዓተ-ፆታ ደንቦችን፣ ባህላዊ ልምዶችን፣ የቤተሰብ ድጋፍን እና የማህበራዊ አውታረ-መረቦችን ተደራሽነት እና ተፅእኖ ይመረምራል፡፡ በፍትህ ረገድ ሴቶችን ስለማበቃት ደግሞ የህግ እና የዳኝነት ስልጣን፣ የሴቶች ፍትህ የማግኘት መብትን፣ የህግ ግንዛቤን፣ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን መከላከል እና የህግ መብቶችን ማስከበርን ይመለከታል። በመጨረሻም ሰላም እና ደኅንነት የሴቶችን ከግጭት እና ከጥቃት የመጠበቅ መብትን፣ በሰላም ግንባታ ሂደቶች ውስጥ ሴቶች ያላቸውን ተሳትፎ እና አጠቃላይ ደህንነታቸውን በሕዝብ እና በግል ጉዳዮች ውስጥ ስላላቸው ሚና ያቀነቅናል።



ምንጭ፡ ከካቢር (N. Kebeer 1999) የተወሰደ

# 2 በጥናቱ የተዳሰሱ ጭብጦችና የተገኙ ውጤቶች

እስካሁን እንደተገለጸው የሴቶችን አሁናዊ ሁኔታ እና ፍላጎቶችን ለመዳሰስ የተለያዩ ጭብጦች በጥናቱ ተካተዋል። እነዚህም ጭብጦች ከኢኮኖሚያዊ ጀምሮ የሴቶች ጤና፣ ሰላም እና ደህንንት እና የመሳሰሉት ናቸው። በመቀጠልም ሌሎች ጉዳዮችም፣ ማለት፣ ተግደሮት እና ተገዳሮትን ስለመቋቋም እና የመሳሰሉት በዚህ ክፍል የተካተቱ ናቸው። በመጀመሪያ በሴቶች ህይወት ዙርያ የሚያጠነጥኑ ቅልፍ ጭብጦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 2.1 ቁልፍ ጭብጦች በሴቶች ህይወት

### 2.1.1 የሴቶች የኢኮኖሚ ሁኔታ

- ጥናቱ እንደሚያሳየው በሴቶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ላይ መጠነኛ መሻሻል ቢታይም በሁለቱ ጾታዎች መካከል አሁንም ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አለ። አብዛኛዎቹ ሴቶች በግል ስራ ወይም ክፍያ የሌለዉ የቤት ውስጥ ስራ ላይ የተሰማሩ ናቸው። ከዳሰሳ ጥናቱ በፊት በነበሩት 7 ቀናት ውስጥ ስለስራቸው የተጠየቁት ሴቶች 27.3 በመቶው ገቢ በሚያስገኝ ስራ ተቀጥረው የሚሰሩ (productive economic employment) ሲሆን 41.3 በመቶው ግን ምንም ክፍያ በሌለው በቤት ውስጥ ስራ እና 17.8 በመቶው ደግሞ በሁለቱም ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ ናቸው። ይህ ማለት በአጠቃላይ 45.1% ያህሉ ሴቶች ብቻ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል ማለት ነው። ይህ ውጤት የሠራተኛ ኃይል እና የፍልሰት ዳሰሳ ጥናት (Labor Force and Migration Survey፡ ማለትም LMS (ESS, 2021)) ውጤት ጋር ተቀራራቢ ነው። ይህም ማለት፣ ይህ የተጠቀሰው ጥናት ከመካሄዱ በፊት በነበሩት 7 ቀናት ውስጥ ገቢ በሚያስገኝ የስራ ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ የሴቶች ቁጥር 42.4% ነበር።
- በሁሉም የእድሜ ምድቦች፣ ክልሎች እና የአመራርነት ደረጃዎች ውስጥ ባሉ ሴቶች ምግብ ማብሰል እና ምግብ ማዘጋጀት በጣም የተለመዱ የቤት ውስጥ ተግባራት ሲሆኑ 82.5% የሚሆኑት ሴቶች ይህን ስራ ይሰራሉ። በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰው እና 4.1% ሴቶች የተሰማሩበት የቤት ውስጥ ስራ ደግሞ ቤትና የቤት እቃዎችን ማጠብ/ማስተካከል ነው።
- 59.6% የሚሆኑ ሴቶች የመኖሪያ ቤት እንዳላቸው ጥናቱ ያሳያል። ከእነዚህ ቤት ካላቸው ሴቶች አብላጫው ማለትም 75.0% የጋራ ባለቤትነት ያላቸው ናቸው። ሌሎች 19.8% የግል የባለቤትነት መብት ያላቸው ሲሆን 5.3% ደግሞ የግልም የጋራም ባለቤትነት መብት ያላቸው ናቸው።
- 40.4% የሚሆኑ ሴቶች የእርሻ መሬት ይዞታ ያላቸው ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ 74.8% የሚሆኑት የጋራ፣ 21.7% የግል እና 3.6% ደግሞ የጋራም የግልም ይዞታ ያላቸው ናቸው። 15.0% የሚሆኑ ሴቶች ለእርሻ መሬታቸው ምንም አይነት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ የሌላቸው ሲሆኑ 61.1% የሚሆኑት የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አለን ብለዋል።
- አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊ ሴቶች የግብርና ግብዓቶችን እንደሚጠቀሙ ተናግረዋል። ይህም 67.7% የሚሆኑት ምርጥ ዘር፤ 65.5% የአፈር ማዳበሪያ፣ 60.9% ፀረ-ተባይ መድሃኒቶች፤ እና 51.7% የሚሆኑት የእርሻ በሬ እንደሚያገኙ/እንዳላቸው ተናግረዋል። በተጨማሪም 51.5% የሚሆኑት ስለአፈር እና ውሃ ጥበቃ ግንዛቤ እንዳላቸው ተናግረዋል። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛዎቹ ሴቶች ማለትም 73.6% የመስኖ እርሻ ተደራሽነት የላቸውም፣ 62.3% የሚሆኑት ሴቶችም የኤክስቴንሽን መርሃግብር አገልግሎቶች የላቸውም።

**የሴቶች የኢኮኖሚ ሁኔታ**

| 27.3% | 41.3% | 17.8% |
|---|---|---|
| ገቢ በሚያስገኝ ስራ ተቀጥረው የሚሰሩ | ምንም ክፍያ በሌለው በቤት ውስጥ የሚሰሩ | ገቢ በሚያስገኝ እና ክፍያ በሌለው የሚሰሩ |

- በአጠቃላይ ሲታይ ምንም እንኳን ጥቂት ሴቶች በንብረቶቻቸው እና ገንዘብ ላይ የጋራ የውሳኔ ሰጪነት ሚና ቢኖራቸዉም፤ ብዙ ሴቶች፣ በተለይ ወንዶች አባወራ በሆኑበት ቤተሰብ ውስጥ፣ በንብረት አጠቃቀም ወይም አያያዝ ዙርያ የውሳኔ ሰጭነትን ሚና አያገኙም። በተለይ ያገቡ ሴቶችን ያየን እንደሆነ ግን አብዛኞቹ ያገቡ ሴቶች ንብረት ላይ ከባሎቻቸው ጋር በጋራ ውሳኔ የመስጠት እድል እንዳላቸው ተናግረዋል። ከዚህም ውስጥ 83.5% የሚሆኑ ሴቶች ቤት/ንብረቶቻቸውን አስይዘው መበደር ቢፈልጉ ከባላቸው ጋር የጋራ ውስኔ መስጠት እንደሚችሉ የተናገሩ ሲሆን 92% የሚሆኑት እንዲሁ ከሽጭ የሚገኘው ገቢ አያያዝ/አጠቃቀም ላይ ከባሎቻው ጋር በጋራ መወሰን እንደሚችሉ ተናግረዋል።
- 12.7% የሚሆኑት ያገቡ ሴቶች ባሎቻቸውመሬታቸውን ማስያዣ አድርገው መበደር ሲፈልጉ ውሳኔው ላይ ምንም ተሳትፎ እንደማይኖራቸው የገለጹ ሲሆን 9.7% የሚሆኑት ደግሞ መሬትን በውርስ አሊያም በሌለላ መንገድ ለሌላ ወገን ለማስተላፍም ሆነ ለማከራየት የሚደረግ ውሳኔ ላይ ተሳትፎ እንደሌለላቸው ተናግረዋል።
- በተጨማሪም ካገቡ ሴቶች ውስጥ በአብዛኛው (ማለትም 33.1% የሚሆኑት ራሳቸው ያመነጩት ገቢ ላይ፣ 33.6% የሚሆኑት ከትዳር አጋራቸዉ ከሚገኝ ገቢ ላይ፣ 32.3% የሚሆኑት ለቤታቸው የሚፈጸሙ ትልልቅ ግዥዋች ላይ፣ 29.4%ቱ በሽያጭ ጉዳዮች ላይ እንዲሁም 24% የሚሆኑት ብድር-ነክ ጉዳዮች ላይ የውሳኔ ሰጭነት ሚና የላቸውም።
- በወንዶች የሚመሩ ቤተሰቦች (male headed households) ውስጥ 42.8% የሚሆኑት ሴቶች የእርሻ መሬት ይዞታ ባለቤትነት መብት አለን ያሉ ቢሆንም 4.1-12.7% የሚሆኑት ያገቡ ሴቶች በግብርና መሬትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ከመስጠት የተገለሉ ናቸው። በተጨማሪም 33.1% የሚሆኑት ያገቡ ሴቶች ከተለያዩ ገቢ ማመንጫዎች (income generating activities) የተገኙ ገቢዎች ላይ ውሳኔ መስጠት አይችሉም። በተጨማሪም በጋብቻ ውስጥ ካሉ ሴቶች ውስጥ 2.8% የሚሆኑት ከመደበኛ ምንጮች (formal sources) አማካይነት ብድር ተጠቃሚ የሚሆኑ ሲሆን ነገር ግን ከእነዚህ ዉስጥ 24.0% የሚሆኑት የተበደሩትን ገንዘብ ምን ላይ ማዋል እንዳለባቸው ውሳኔ መስጠት አይችሉም። ይህ የሚያሳየው ሴቶች በሃብት፣ ንብረት እና ፋይናንስ ባለቤትነት እና አጠቃቀም ላይ ውስንነት ያለባቸው መሆኑን ሲሆን ይህም ሴቶችን ለማብቃት (women empowerment) የሚደረገው ጥረት ገና መሆኑን ያሳያል።
- በጥናቱ ላይ ተሳታፊ ከሆኑት ሴቶች አብዛኞቹ (ማለትም 57.3) የባንክ ሂሳብ የላቸውም። ቀሪዎቹ የባንክ ሂሳብ ያላቸው ሴቶች 38.4% የሚሆኑት በግል 4.3% ደግሞ በጋራ ያላቸው ናቸው።
- ሴቶች በማህበራት ውስጥ ያላቸው አባልነት ተሳትፎም ዝቅተኛ ነው። አባል ከሆኑት ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው (ማለትም 9.6%) በሴቶች ማህበራት ውስጥ ያላቸው የአባልነት ተሳትፎ ሲሆን 4.3% የሚሆኑት በራስ-አገዝ ማህበራት (self-help groups)፣ 2.4% የሚሆኑት በወጣቶች ማህበራት፣ 1.5% የሚሆኑት በሙያ ማህበራት


እና 1.4% የሚሆኑት በንግድ ማህበራት በአባልነት ደረጃ ይሳተፋሉ። ጥናቱ እንደሚያሳየው በንጽጽር ሲታይ ሴቶች በሴቶች ማህበራት ለመሳተፍ የተሸለ ዝንባሌ ያላቸው ቢሆንም በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎ ሲታይ ግን አሁንም እንዳልተሻሻለ ያሳያል። በዚህ ጥናት ተሳታፊ ከሆኑት ሴቶች በአብዛኛው ለተለያዩ ድንገተኛ ችግሮች (shocks) መጎዳታቸውን ገልጸዋል። ይህም 60.3% የሚሆኑት የምግብ ዋጋዎች መናር፣ 42.6% የተለያዩ ግብዓቶች ዋጋ መናር አሊያም የእነዚህ ግብዓቶች አለመኖር፣ 20.9% የሚሆኑት በአካቢያቸው ላይ በሚፈጠር ብጥብጥ፣ 20.8% የሚሆኑት በጦርነት፣ 14.4% የሚሆኑት በድርቅ እና 13.1% የሚሆኑት በቤተሰብ ውስጥ በሚፈጠር የጤና መጓደል/ህመም ይጠቃሉ። በቅደም ተከተል ያሉት ሁለቱ ዋና ዋና ድንገተኛ ችግሮችን ውጤት በወንድ-መር እና በሴት መር (women-led) ቤተሰብ ላይ ለይተን ስናይ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው። ይሁንና የችግሮቹ ክብደት እንደሁኔታው ሊለያይ እንደሚችል ማወቅ ይቻላል። ለምሳሌ፣ ጦርነት በሴት-መር ቤተሰብ ላይ የበለጠ አስከፊ እንደሚሆን እሙን ነው።

- የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ጥናቱ በሚደረግበት ወቅት 8.2% የሚሆኑ ሴቶች የምግብ ዋስትና መርሃ-ግብር (production safety-net program) ተጠቃሚ ናቸው። ይህም መርሃ-ግብሩ ካስቀመጠው 10% የሚሆኑ በተለይም የምግብ አጠር የሆኑ ወረዳዎች እና ቤተሰቦችን ተጠቃሚ የማድረግ ግብ ጋር የሚጣጣም ነው። ከዚህ መርሃ-ግብር ተጠቃሚነት በተጨማሪ፣ 11.5% የሚሆኑ ጥናቱ ላይ የተሳተፉ ሴቶች ይህ ጥናት ከመካሄዱ በፊት በነበሩ 12 ወራት የሰብአዊ እርዳታ ተጠቃሚ እንደሆኑ ተናግረዋል።
- ከላይ ከተገለጹት መጠናዊ (quantitative) ውጤቶች በተጨማሪ የአይነታዊ (qualitative) ጥናት ውጤቶችም ሴቶች በኢኮኖሚው ዘርፍ እንዳይበቁ እንቅፋቶች እንዳሉባቸው ያሳያሉ። እነዚህ እንቅፋቶች በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ እና በማህበረሰብ ደረጃ ያሉትን የሚያጠቃልል ሲሆን ለምሳሌ ያህል የራዕይ ውስንነት፣ ጊዜን በአግባቡ አለመጠቀም፣ እና የቤት ውስጥ ጫናዎችን እና ሃላፊነቶችን ከወንዶች ጋር አለመጋራት መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ችግሮች በአዲስ አበባ፣ በአሶሳ እና በሌሎችም አካባቢዎች በተደረጉ የቡድን ውይይቶች ተንጸባርቀዋል። በአርባ ምንጭ ዙርያ ወረዳ በተደረገው የቡድን ውይይት የተሳተፉ ሴቶች ደግሞ የቢዝነስ ሃሳቦችን በተመለከተ፣ ስልጠናዎች አለማግኘት እና የገንዘብ ምንጮች ውስንነቶችን በተጨማሪ አንደመሰናክል አብራርተዋል።
- በተጨማሪም ግጭቶች ገበያና መሠረተ ልማትን በማወክ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በማባባስ የሥራ አጥነት መጠንን ከፍ ያደርጋሉ። በበመቀሌ፣ሀውዜን እና ሃገረሰላም ወረዳዎች (ትግራይ ክልል) የተደረጉ የቡድን ውይይት የውጤቶች እንደሚያመለክቱት ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ የቤተሰብ መቃወስ እና በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች በሴቶች የሚመሩ ቤተሰቦች መበራከታቸው የሴቶችን ተግዳሮቶች እያወሳሰቡ ናቸው።

## 2.1.2 የጤና ሁኔታ

- አብዛኞቹ ሴቶች (73.6%) የጤና አጠባበቅ አገልግሎት እንደሚያኙ የገለጹ ሲሆን እንደገና 81.5% የሚሆኑት ደግሞ የሴቶች ጤና እንክብካቤ አገልግሎት ስለመኖሩ ግንዛቤ አላቸው።
- በጤና አጠባበቅ መሠረተ ልማቶች ላይ በተለይም ከጦርነቱ በኋላ ባሉ ቦታዎች፣ በገጠር እና ብዙ አገልግሎት በሌላቸው አካባቢዎች የሴቶች የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተደራሽነት ላይ ችግሮች አሉ። በቡድን ውይይቶች የተገኘው የአይነታዊ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች የጤና አጠባበቅ አገልግሎቶቹ ተደራሽ ናቸው። ነገር ግን በእነዚህ ቦታዎችም ጭምር የመሰረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት እጥረት እና የዋጋ ንረት ችግሮች አሁንም ተግዳሮት ሁነው እንደቀጠሉ ነው። በትግራይ፣ በተለይም ተፈናቃዮች በተጠለሉባቸው ቦታዎች፣ ሴቶች በመድኃኒት እጥረት እና በቂ አገልግሎት ባለማግኘታቸው ምክንያት የጤና አገልግሎታቸው ውስን ነው።
- እንደጥናቱ ተሳታፊዎች ከሆነ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ከፍተኛ ዋጋ (30.2%) እና የጤና መድህን እጥረት (26.3%) በተለይ ለሴቶች የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ትልቅ እንቅፋት ሆነዋል። በተጨማሪም የትራንስፖርት እጦት (15.1%) እና ረጅም ወረፋ (10.9%) የጤና እንክብካቤን ለማግኘት ከፍተኛ እንቅፋት የሆኑ ችግሮች ናቸው። ችግሩ በገጠር ጎልቶ ታይቷል።
- 36.3% የሚሆኑት ሴቶች ጥናቱ ከተካሄደበት ጊዜ ቀደም ብሎ ባሉት 12 ወራት ውስጥ ኤችአይቪ/ኤድስን ጨምሮ የጾታዊ እና የስነ ተዋልዶ ጤናን በተመለከተ መረጃ እንደደረሳቸው ተናግረዋል።
- የአይነታዊ ጥናት ውጤት በአጽንኦት እንደሚያመለክተው፣ ሴቶች የግበረ-ስጋ ግንኙነት እና የስነ ተዋልዶ ጤናን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ተግዳሮቶች እንዳሉ ያሳያል። ባህላዊ ልማዶች እና የጤና ባለሞያዎች አመለካከት በእነዚህ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ግልጽ ውይይት እንዳይኖር ምክንያት ሆነዋል። በተላይም ስለእነዚህ ጉዳዮች በገጠር አካባቢ ማውራት እንደ ነውር ስለሚቆጠር ችግሩ የከፋ ነው።
- ጥናቱ እንደሚያሳየው፣ በአሁኑ ጊዜ 60.7% የሚሆኑ ሴቶች የሆነ አይነት የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ ነው። ነገር ግን ይህ አሃዝ ከክልል ክልል ከፍተኛ ልዩነት አለው። በተለይ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የወሊድ መቆጣጠሪያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር 80.4% ሲሆን በአዲስ አበባም 73.5% ነው። በአንጻሩ ሶማሌ ክልል ደግሞ የተጠቃሚዎቹ ቁጥር ከ 20.5 በመቶ ያነሰ ነው።

- የዳሰሳ ጥናቱ በመውለጃ ዕድሜ (15-49) ክልል ውስጥ ባሉ ሴቶች ላይ ስለተለያዩ የንፅህና መጠበቂያ ፓዶች መረጃ ይሰጣል። በዚህ መሰረት፣ 57.7% የሚሆኑ ሴቶች ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ ውለው የሚጣሉ (disposable) ፓዶችን እንጠቀማለን ያሉ ሲሆን፣ 9.3% ሴቶች ደግሞ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉትን (recyclable) እና 29.2% እዚያው በአካባቢያው የተሰሩ ፓዶችን እንጠቀማለን ብለዋል። አንዴ ብቻ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ የሚጣሉትን ፓዶች ላለመጠቀም እንቅፋት ናቸው የተባሉት ጉዳዮች የተደራሽነት ችግር (42.9%) እና ተመጣጣኝ ያልሆነ ዋጋ (17.1%) እና የግንዛቤ ማነስ ችግሮች (27.2%) ናቸው።




## 2.1.3 የትምህርት ተደራሽነት

- የሴቶች የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ምጣኔ (literacy rate) 55.1% ሲሆን ከሰሃራ በታች ካሉ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት አንጻር እንኳን ሲታይ ዝቅተኛ ነው። ለምሳሌ፣ እንደ ኬንያ እና ደቡብ አፍሪካ ባሉ ሀገራት የሴቶች የማንበብና መጻፍ ምጣኔ ከ70 % በላይ ነው።
- ማንበብና መጻፍ ከሚችሉት ሴቶች ውስጥ 76.3% የሚሆኑት ከ15-29 እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሁነው ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። በአንጻሩ እድሚያቸው በ50+ የእድሜ ክልል ውስጥ ካሉት ሴቶች ደግሞ ማንበብና መጻፍ የሚችሉት 17.1% ብቻ ሁነው ዝቅተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። እንዲሁም በከተማ ያሉ ሴቶች ከገጠር አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀሩ ማንበብና መፃፍ የመቻል እድላቸው ሰፊ ነው።
- ስለቴክኖሎጂ ያላቸውን ክህሎት በተመለከተ 15% የሚሆኑት ሴቶች ስለ ኮምፒዩተር አጠቃቀም ያውቃሉ። እንዲሁም 21.8% የሚሆኑት ኢንተርኔት መጠቀም የሚችሉ ሲሆኑ 53.8% ደግሞ የሞባይል ስልክ ባለቤት ናቸው።
- በጥናቱ መሰረት 45.3% የሚሆኑ ሴቶች የሚፈልጉትን ያህል በትምህርት እንዳይገፉ ተግዳሮት እንደገጠማቸው ተናግራዋል። ቁልፍ ችግሮች ተብለው የተጠቀሱት ከቤተሰብ ድጋፍ አለማግኘት (30%)፣ የገንዘብ እጦት (27.2%) እና የማይከፈልበት የቤት ውስጥ ሥራ ጫና (15.6%) ናቸው።
- ስለ ሴቶች እና ወንዶች እኩል የትምህርት እድል ተጠቃሚነትን በተመለከተ 72.9% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች ለወንዶች እና ለሴት ልጆች እኩል የትምህርት እድል እንደሚያሰፈልጋቸው ያምናሉ። በሌላ መልኩ ደግሞ 10.9% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች የተሻለ የትምህርት እድል የሚያስፈልገው ይልቁንም ለወንድ ልጆች ነው ብለዋል። ሌሎች 10% የሚሆኑት ደግሞ የተሻለ እድል የሚያስፈልገው ለሴት ልጆች ነው ብለዋል።
- የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ መጠን በተለያዩ የሀብት ደራጃ ባላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ የዳሰሳ ጥናቱ አሳይቷል። በተሻለ የሀብት ደረጃ ውስጥ ያሉት የጥናቱ ተሳታፊዎች ብዙዎቹ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ሲሆን ዝቅተኛ የሃብት ደረጃ ያላቸው ተሳታፊች ደግሞ በአብዛኛው ማንበብና መጻፍ አይችሉም።
- ከአሶሳ (ቤንሻንጉል ጉሙዝ) እና ከባህርዳር (አማራ) የተገኙ የአይነታዊ ጥናት ውጤቶች እንደሚያሳዩት ምንም እንኳን ለውጦች ቢኖሩም አሁንም ሴቶች እና ሴት ልጆች በትምህርት ስኬታማነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በርካታ ምክንያቶች አሉ ። እነዚህ ምክንያቶች በሥርዓተ-ፆታ ዙርያ ያሉ የተዛቡ አመለካከቶች፣ ባህላዊ ወጎች እና ልምዶች፣ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ እና ያለዕድሜ ጋብቻ ናቸው። ተጋላጭ የሆኑ የህበረተሰብ ክፍሎች፣ በተለይም አካል ጉዳተኛ እና ሴቶች ደግሞ ተጨማሪ እንቅፋቶች ያጋጥማቸዋል። የማይከፈልበት የቤት ውስጥ ስራ (unpaid care work) በአብዛኛዎቹ የውይይት ቡድኖች ውስጥ እንደፈተና ጎልቶ የተነሳ ምክንያት ነው።
- የሰመራ፣ ሎግያ እና ዱብቲ (አፋር) የየቡድን ውይይት ተሳታፊዎች እንዳሉት የብሄረሰባቸው ባህል ከሴቶች ትምህርት ይልቅ እንደ ያለእድሜ ጋብቻ አይነት ባህላዊ ደንቦችን ማክበር ላይ ትኩረት ይሰጣል። በባህር ዳር (አማራ ክልል) ደግሞ ለሴቶች ትምህርት ተግዳሮቶች ናቸው ተብለው የተለዩት ትምህርት ቤቱ ከቤታቸው ያለው ረጅም እርቀት እና ግጭቶች ይገኙበታል። በተግራይ ደግሞ ጎልቶ የተነሳው ጦርነት እና በጦርነት ምክንያት የትምህርት ቤቶች መውደም ነው።

## 2.2 ተግዳሮቶች እና ተግዳሮቶችን ስለመቋቋም

### 2.2.1 ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች

- ጥናቱ ከመደረጉ አስቀድሞ በነበሩ 12 ወራት ውስጥ ጾታን መሰረት ያደረጉ ሁሉንም አይነት ጥቃቶች እንደተከሰቱባቸው 20.2% የጥናቱ ተሳታፊዎች ሪፖርት አድርገዋል። በዚህም ረገድ የሲዳማ፣ የአፋር፣ የአማራ እና የትግራይ ክልሎች ቀዳሚ ናቸው።
- አካላዊ ጥቃቶችን በተመለከተ ጥናቱ ከተደረገበት ጊዜ አስቀድሞ በነበሩት 12 ወራት ውስጥ 9.3% የሚሆኑ ሴቶች አካላዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል። ከጥቃት ፈጻሚዎች ደግሞ በአብዛኞቹ የተጠቀዎቹ የቅርብ አጋሮች ሲሆኑ ባሎች ወይም ጓደኞቻው ደግሞ ከእነዚህም ግንባር ቀደሞች ናቸው።
- ከጾታዊ ጥቃት አንፃር ሲታይ 6.0% የሚሆኑ ሴቶች ጥናቱ ከመደረጉ በፊት በነበሩት 12 ወራት ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የወሲብ ጥቃት አይነት አጋጥሟቸዋል። ይህም ከDHS 2016 (6.5%) የጥናት ውጤት ጋር ተቀራራቢ ነው። የዳሰሳ ጥናቱ በተለያዩ የስነ-ልቦና ጥቃት ዓይነቶች ላይ መረጃ ሰብስቦ ይህ ጥናት ከመደረጉ በፊት በነበረው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ 13.3% ሴቶች አንድ ወይም ከዚያ በላይ የስነ-ልቦና ጥቃት አይነት ደርሶባቸዋል። ከኢኮኖሚ ጥቃት አንፃር ደግሞ ሲታይ 5.8% የሚሆኑ ሴቶች በተጠቀሰው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የኢኮኖሚ ጥቃቶች አጋጥሟቸዋል።
- ጥናቱ እንዳመለከተው 14.0% የሚሆኑ ሴቶች ያጋጠማቸውን ጥቃት ተከትሎ እርዳታ ለመጠየቅ ሞክረዋል። ነገር ግን ከእነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት (55.2%) ምንም አይነት እርዳታ ሊያገኙ አልቻሉም።
- በአጠቃላይ 81.0% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች ስለ ሴቶች ግርዛት ሰምተዋል፤ 48.5% የሚሆኑት ደግሞ የተገረዙ ናቸው። ከፍተኛው የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት ያለው ሶማሌ (83.5%) እና አፋር (70.2%) ክልሎች ነው።
- በትግራይ ክልል የተደረጉ የቡድን ውይይቶች እንደሚያሳዩት፣ በትጥቅ ግጭቶች ወቅት ሴቶች ላይ የሚደረሱ ሁሉን ዓይነት ጥቃቶች ጨምረዋል። ይህም የትጥቅ ግጭት በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጫና የከፋ እንደሚያደርገው ያሳያል።
- ጥናቱ ጦርነት በተከሰተባቸው እና በተፈናቀሉ አካባቢዎች ለወሲባዊ እና ጾታን ተኮር ያደረጉ ጥቃቶች የተደረገውን ግብረ-መልስም አመልክቷል። በመቀሌ እና ሀውዜን የተደረጉ የቡድን ውይይት ውጤቶች እንደሚያሳዩት ባለድረሻ አካላት ለመሰል ጥቃቶች በቂ ምላሽ አልሰጡም። እነዚህን ጥቃቶች የሚፈጽሙ ግለሰቦችን ተጠያቂ አለማድረግ ብቻ ሳይሆን ለተጎጂዎችም የሚያስፈልገውን የስነ-ልቦና ድጋፍ፣ ምግብ እና መጠለያ ማቅረብም አልተቻለም።

### 2.2.2 የስልቦናዊ ደህንነት እና ጉዳቶችን መቋቋም

ይህ ጥናት የሴቶችን የተለያዩ የስነ-ልቦናዊ እና አዕምሯዊ ደህንነት ጉዳዮችንም ዳስሷል። ለዚህም ማሳያ ተደርገው የተወሰዱት ሴቶች በራሳቸው አቅም ችግሮችን ስለመፍታታ ያላቸው አመለካከት (self-efficacy)፣ ስነ-ልቦናዊ ደህንነት፣ በራስ መተማመን፣ በኑሯቸው ያላቸው የእርካታ ደረጃ፣ እና የጭንቀት ደረጃዎች (stress levels) ናቸው።ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ችግሮችን በራስ አቅም ለመፍታት ስለመቻል የሚለውን መጀመሪያ ስንመለከት ውጤቱ አወንታዊ ነው። ለዚህ የተገኘው አማካይ (mean value) ዝቅተኛው 12 ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 60 ነው። የዚህ ደግሞ አማካይ ውጤት 48.8 ስለሆነ ሴቶች ችግሮችን በራስ አቅም ስለመፍታት ያላቻው ግንዛቤ አወንታዊ ነው ማለት ነው። ነገር ግን የቡድን ውይይት ውጤት እንደሚያሳየው ከሆነ በተለያዩ አካባቢዎች የተንሰራፉት ኢ-እኩልነቶች አሁንም ሴቶች በራሳቸው ችሎታ ያላቸውን መተማመን ሸርሽሯል። ለምሳሌ፣ የሎግያ (አፋር) ተሳታፊ ሴቶች በራሳቸው ብቃት እንዳይተማመኑ አሁንም በባህላቸው የተንሰራፋው የኢ-እኩልነት እና አድልዎ ጫና እንደሚያሳድርባቸው ተናግረዋል። በተመሳሳይ በኦሮሚያ-ሞቱ የተደረጉ ውይይቶችም ከጎጂ ልማዶች የሚመነጩ የስነ-ልቦናዊ ጥቃቶች ሴቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርሱ ተናግረዋል።
- ይህ ጥናት ሴቶች በኑሯቸው ላይ ያላቸውን እርካታ ለመለካት ከቤተሰብ፣ ከጓደኞች፣ ከስራ፣ ከገቢ፣ ሴቶች በሚኖሩበት ቤት እና በአጠቃላይ ህይወት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ዙርያ መደበኛ የልኬት ዘዴን ተጠቅሟል። በዚህም መሰረት የጥናቱ ግኝት 27.7 አማካኝ ውጤት (mean score) የሚያሳይ ሲሆን ይህም ማለት በስድስቱ እርካታን ለመለካት ጥቅም ላይ ከዋሉ ጉዳዮች ዙርያ መካከለኛ የእርካታ ደረጃ (moderate level of satisfaction) እንዳላቸው ያሳያል። ዝቅተኛው እና ከፍተኛው አማካይ ዋጋ (mean values) በቅደም ተከተል 7 እና 49 ናቸው።
- የኢትዮጵያ ሴቶችን የጭንቀት ደረጃ ለመለካት ደግሞ እንደ የስራ እድል፣ የፋይናንስ መረጋጋት፣ ተስማሚ አጋር ማግኘት እና ያልተጠበቁ ወጪዎችን መጋፈጥ ባሉ የተለያዩ አመላካች ሁኔታዎችን በማካተት ለመለካት ተሞክሯል። በጥናቱ መሰረት አማካኝ ውጤቱ (average score) 14.6 ሲሆን ይህም በአምስቱ ጭንቀትን ለመለካት ጥቅም ላይ በዋሉ ዘርፎች ከፍ ያለ ጭንቀት እንዳለባቸው ያመለክታል። ዝቅተኛው አማካኝ ዋጋ (mean score) 5 ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 25 ነው።
- ጥናቱ በኢትዮጵያ ሴቶች መካከል ያለውን ስነ ልቦናዊ ደህንነት እና በራስ መተማመንንም ለመለካት ሞክሯል። ውጤቶቹ እንደሚያሳዩት አማካኝ ዋጋ (mean score) 23.6 ሲሆን ዝቅተኛው 12 ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 60 ነው። ይህ የሚያመለክተው የኢትዮጵያ ሴቶ መጠነኛ የሆነ (moderate) የስነ-ልቦና ደኅንነት እና ለራስ ከፍ ያለ ግምት እንዳላቸው ነው።

### 2.2.3 የፍትህ ተደራሽነት

- ጥናቱ ከመደረጉ አስቀድሞ በነበሩት12 ወራት ውስጥ የሙግት ጉዳዮችን (disputes) ሪፖርት ያደረጉ ሴቶች አጠቃላይ 5.1 በመቶ ናቸው። የእነዚህ ሙግቶች ምክንያቶች ደግሞ ከመሬት ጋር የተያያዙ (21%)፣ የቤተሰብ አባላት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች (45%)፣ ፍቺ (9.5%)፣ እና ከንብረት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ይጠቀሳሉ። እነዚህ ክርክሮች በገጠር እና በከተማ ሲነጻጸር በከተማ ያሉ ሴቶች 5.9% ክርክር ውስጥ የገቡ ሲሆን በገጠር 4.7% ደግሞ ያሁሉ ናቸው።
- ሙግት ካጋጠማቸው ሴቶች መካከል 45% የሚሆኑት አለመግባባቱን ለመፍታት ድጋፍ አግኝተዋል። የአካባቢ ሽምግልና (61.8%) በጣም ጉልህ የሆነ የድጋፍ አይነት ሲሆን፣ ከዚያም የህግ አገልግሎት (21.4%) እና የህግ እርዳታ (12.6%) በቀደም ተከተል ሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃ ይይዛሉ።
- ድጋፍ ካገኙት መካከል 66.6% ያህሉ ረክተዋል ቢባልም 21.2% ያህሉ ግን ባገኙት ድጋፍ ምንም እርካታ አልተሰማቸውም።

## 2.3 ፍላጎት እና ውክልና (aspirations and agency)

ይህ ክፍል ሴቶች ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች፣ በመንግስት አስተዳደር መዋቅሮች ውስጥ ስለሚኖራቸው ሚና ፣ የፖለቲካ እና የሲቪክ ተሳትፎን እና ስለ ሰላምና ደኅንነት ያላቸውን ምኞት (aspirations) እና ራስን መወከል (agency) ይዳስሳል።

### 2.3.1 ሴቶች ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች እና ምኞቶች

- ጥናቱ ላይ ከተሳተፉት ሴቶች ውስጥ 69.30% የሚሆኑት በመንግስታዊ አስተዳደር ውስጥ ለመሳተፍ ያላቸው ፍላጎት/ምኞት ዝቅተኛ ወይም በጣም ዝቅተኛ ሲሆን 13.8% የሚሆኑት ብቻ ከፍተኛ ምኞት እንዳላቸው ተናግረዋል። ብዙዎቹ ሴቶች የመንግስት/የፖለቲካ ስልጣን (power) የሌላቸው ስለመሆኑ የገለጹ ሲሆን በዚህ ላይ ተሳትፎ ለማድረግ የሚረዳ መንገድ ምን እንደሆነም አያውቁም። ከላይ እንደተገለጸው 13.80% የሚሆኑ ሴቶች በስልጣን እና መንግስት አስተዳደር ላይ ለመሳተፍ ያላቸው ምኞት ከፍተኛ እንደሆነ ገልጸው ለዚህም እንዲበቁ ሴቶች የተለያዩ መሰናክሎችን በጣጥሰው ማለፍ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።
- ከላይ እንደተገለጸው ጥናቱ ሴቶች ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮችም ለይቷል። በዚህም መሰረት 71.6% የሚሆኑ ሴቶች ለሰላም እና ደህንነት ቅድሚያ እንዲሰጥ የሚፈልጉ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለኢኮኖሚያ እድሎች (economic opportunities) 61.1% የሚሆኑ ሴቶች ቅድሚያ እንዲሰጠው ይፈልጋሉ። ለጤና አገልግሎት (55.5%)፣ መሠረተ ልማቶች እና መሰረታዊ አገልግሎቶች (36.2%)፣ ለማህበራዊ ደህንነት እና የድጋፍ አውታሮች (17.8%) እና በፖለቲካ ተሳትፎ (2.4%), ሌሎች ጉዳዮች (0.4%) ሴቶች ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች ናቸው።

### 2.3.2 ፖለቲካዊ እና ህዝባዊ ተሳትፎ

- የኢትዮጵያ ሴቶች ስለህጎች እና ፖሊሲዎች ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት፣ የጥናቱ ተሳታፊዎች የተሻለ ግንዛቤ አላን ያሉት ስለ ህገ-መንግስቱ ነው። በዚህም መሰረት 52.40% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች በህገ-መንግስቱ ውስጥ ስለ ሴቶች የተካተቱ መብቶችን እንደሚያውቁ ተናግረዋል። በመቀጠልም ስለ መሬት ህጎች እና የወንጀል ህግ 48.90% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታዎች፣ ስለቤተሰብ ህግ እና የሴቶች መብቶች 45.90% እና ስለሴቶች ፖሊሲ 35.60% የሚሆኑ ሴቶች ግንዛቤ እንዳላቸው ተናግረዋል። ስለሠራተኛ ሕግ ዝቅተኛው የግንዛቤ ደረጃ (24% የጥናቱ ተሳታዎች ብቻ) ታይቷል።
- በዳሰሳ ጥናቱ መሰረት ወደ ግማሽ የሚጠጉ የጥናቱ ተሳታፊዎች ስለሕጎች ቢያንስ የተወሰነ ግንዛቤ እንዳላቸው ቢጠቁሙም፣ በቡድን ውይይቱ ላይ ተሳታፊ የሆኑ ሴቶች (ለምሳሌ አሰሳ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል) ስለ ህጎች ያላቸው ግንዛቤ አንስተኛ ከመሆኑ የተነሳ በገጠር መሬት አጠቃቀም እና በትዳር ዙርያ ያላቸውን መብት እንኳ ለማስከበር ይቸገራሉ።

- 84.1%፣ 35.8% እና 44.5% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች በቅደም ተከተል የጠቅላይ ሚኒስትሩን፣ በወቅቱ የነበሩትን ፕሬዚዳንቷን እና የገዢውን ፓርቲ ስም እንደሚያውቁ ተናግረዋል።
- በዳሰሳ ጥናቱ መሰረት 53.1% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታዎች ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ መሪዎች ናቸው የሚለውን ሀሳብ የሚቃወሙ ሲሆን 34.4% የሚሆኑት ደግሞ አሁንም ወንዶች ከሴቶች ይልቅ የተሻሉ መሪዎች ናቸው ብለው ያምናሉ። እንዲሁም 67.2% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች ሴቶች በከፍተኛ ሃገራዊ ይሰልጣን ቦታ ቢመረጥ ጥሩ ነው ብለው የሚያምኑ ሲሆን 71% ደግሞ ሴቶች ለወረዳ ሊቀመንበርነት ቢመረጡ ተገቢ ነው ያሉ ናቸው።
- በሚቀጥለው ምርጫ 77.1% የሚሆኑ የዳሰሳ ጥናቱ ተሳታፊዎች ድምጽ ለመስጠት እቅድ እንዳላቸው እና 71.6% የሚሆኑት ባለፈው ምርጫ ተመዝግበው ድምጽ መስጠታቸውን አረጋግጠዋል። ባለፈው ምርጫ ካልመረጡት ውስጥ (n=9162)፣ ላለመምረጣቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ብለው ያሰቀመጡት በወቅቱ እድሜቸው ለመመርጥ የሚፈቅድ ስለልነበረ (49.2%)፣ ድምጽ ለመስጠት ፈቃደኛ ስላልነበሩ (13.1%)፣ የምርጫ ካርድ በወቅቱ ስላልወሰዱ (10.2%)፣ ህመም (8.3%)፣ ድምጽ ለመስጠት ጊዜ ማጣት (5.8%)፣ እና በምርጫ ጣቢያዎች የሚደርስ ብጥብጥ በመስጋት (3%) ናቸው።
- ሴቶች በተለያዩ አደረጃጀቶ ያላቸውን ተሳትፎ በተመለከተ 8.4% የሚሆኑ ሴቶች የሴቶች የውይይት ቡድን አባላት (women's discussion group)፣ 1.9% የሚሆኑት የወረዳ ወይም የቀበሌ አስተዳደር ወይም ምክር ቤት አባላት፣ 2.1%፣ የአካባቢ ዳኝነት ወይም የወረዳ ምክር ቤት አባላት እና 2.1% ሴቶች የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ነን ብለዋል ።
- በቡድት ውይይት ተሳታፊ የሆኑ ሴቶች እንደገለጹት (ለምሳሌ በሶማሊ ክልል የአውባሬ ወረዳ፣ በአፋር ክልል) የሴቶች ተሳትፎ እየተሻሻለ ቢሆንም ሌሎች የቡድን ውይይቱ ተሳታፊዎች (ለምሳሌ በአሶሳ) የፖለቲካ ሥርዓቱ ግራ የሚያጋባ እና ለተሳትፎም የማያነሳሳ መሆኑን ተናግረዋል።

## 2.3.3 የሰላም እና የደህንነት ሁኔታ

- ስለሰላም ሁኔታ ያላቸውን አመለካከት በተመለከተ 56% የሚሆኑት የጥናቱ ተሳታዎች አካባቢያቸው ሰላማዊ እንደሆነ የሚሰማቸው ሲሆን 10% የሚሆኑት ደግሞ በአጎራባች አካባቢዎች ያለው የሰላም ሁኔታም ቢሆን እየተሻሻለ ነው ብለው ያስባሉ። በአንፃሩ 16.6% ያህሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች ጥናቱ ከመደረጉ በፊት ካለው አንድ አመት ወዲህ ያለውን ጊዜ እንኳን ብንመለከት የሰላም ሁኔታዉ እያሽቆለቆለ ነው ሲሉ፤ 17.2 % ደግሞ ምንም ሰላም የለም ብለዋል። የአማራ ክልልን ምላሽ ለይተን ካየን 52% የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታዎች ምንም ሰላም የለም ያሉ ናቸው።
- ጥናቱ ከመደረጉ በፊት በነበረው አንድ አመት ውስጥ የሰላም ሁኔታው እያሽቆለቆለ ነው ብለው ከሚያምኑት ሴቶች መካከል የትግራይ ሴቶች በ48.4% ሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ።
- ምንም እንኳን አሀዛዊ መረጃዎች ጥሩ ምስል ቢያሳዩም ከአዲስ አበባ፣ ትግራይ፣ ቤኒሻንጉል እና አማራ የተውጣጡ የየቡድን ውይይቱ ተሳታፊ ሴቶች ከደህንነታቸው አንጻር ችግር እንደሚገጥማቸው ተናግረዋል።
- ሴቶች የሚያጋጥሟቸው ዋና ዋና የግጭት ዓይነቶች:- የትጥቅ ግጭቶች (29.5%)፣ የሀብት ግጭት (12%)፣ ብሔር ተኮር ግጭቶች (14.1%)፣ የሀይማኖት ግጭቶች (6%)፣ የወሰን/ድንበር ግጭቶች (16.5%)፣ እና ዘረፋ (13.4%) ናቸው።
- በጥናቱ ተሳታፊ ከሆኑ ሴቶች መካከል 30.2% የሚሆኑት ስለግል እና ስለቤተሰቦቻቸው ደህንነት ሁልጊዜ አሊያም ብዙ ጊዜ (either always or sometimes) እንደሚጨነቁ ሲናገሩ 47.4% የሚሆኑት እምብዛም አይጨነቁም ወይም ምንም የሚያስጨንቃቸው የሰላም/የደህንነት ጉዳይ የለም። የአማራ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና የትግራይ ክልሎች ከትጥቅ ግጭቶች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ሲሆኑ፣ የአፋር ክልል ያሉ ሴቶች ደግሞ በተለይ በዘረፋ ምክንያት ከፍተኛ ፍራቻ እንዳለባቸው ተናግረዋል።
- ጥናቱ እንደሚያሳየው ጥናቱ ከመደረጉ አስቀድሞ በነበረው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ 17.4% የሚሆኑ ሴቶች በክልሉ ባለው የትጥቅ ግጭት የተነሳ ስቃይ እንደደረሰባቸው ተናግረዋል። በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ አማራ እና ትግራይ ክልሎች ያሉ ሴቶች በትጥቅ ግጭት ከፍተኛ ስቃይ ነበራባቸው። የትጥቅ ግጭት ከተጋፈጡት ውስጥ 47.4 በመቶው የተፈናቀሉ ናቸው።
- ሰላምን ለማስፈን በሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ አንስተኛ ነው። ይህም፣ በጥናቱ ከተሳተፉት ውስጥ 0.9% ሴቶች ብቻ እንደ መሪ ወይም አደራጅ የተሳተፉ ሲሆን 15.5% ብቻ ደግሞ በበጎ ፈቃድ የተለያየ አይነት አገልግሎት የሰጡ ወይም እንዲሁ በተሳታፊነት የተገኙ ናቸው። በተጨማሪም 37.7% ሴቶች ሰላምን ለማስፈን በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት እንዳላቸው ሲገልጹ፤ 45.9% የሚሆኑት ግን ፍላጎት አልነበራቸውም ወይም መሳተፍ አልቻሉም።
- ከዳሰሳ ጥናት ውጤት በተጨማሪ ከመቀሌ (ትግራይ) ተፈናቅለው ካምፕ ውስጥ የሚገኙ ተሳታፊዎች ጋር የተደረገው የቡድን ውይይት እንደሚያሳየው እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለይም ሴቶችና ሴት ልጆች ሴት ልጆች ላይ አሳሳቢ የሆነ የጸጥታ እና ደህንነት ችግር አለ። ስርቆት፣ ጾታዊ ጥቃት እና የሚከላከልላቸው አካል አለመኖር (lack of prtetcion) በፍርሃትና ስጋት ድባብ ውስጥ እንደከተታቸው ተናግረዋል።
- ሴቶች ሰላምን ለማስፈን በሚደረጉ ጥረቶች ለመሳተፍ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ቢሆንም፣ በርካታ መሰናክሎች መኖራቸውን ጥናቱ ያሳያል። በባህር ዳር (አማራ) እና በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ (ደቡብ ኢትዮጵያ) የተካሄደው የቡድን ውይይት እንደሚያሳየው የማህበራዊ ደንቦችና ባህላዊ ተግባራት፣ የትምህርት ውስንነት እና የግብአት አቅርቦት ተሳትፏቸውን የሚገድቡ ጉዳዮች ናቸው።



# 3 መደምደሚያ እና ምክረ ሃሳቦች

ይህ ክፍል ከላይ የተቀመጡ የጥናቱ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ የመደምደሚያ እና ምከረ-ሃሳቦችን እንደሚከተለው ያቀርባል።

## በኢኮኖሚ ረገድ

**በሥራ ስምሪት ውስጥ አሁንም የሥርዓተ-ፆታ አለመመጣጠን ስለመኖሩ:-** በሴቶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ላይ መጠነኛ መሻሻል ቢኖረውም፣ አብዛኞቹ ሴቶች በራሳቸው ሥራ ወይም በማይከፈልበት የቤት ውስጥ ሥራ ላይ የተሰማሩ ናቸው። ይህም ሴቶች ምርታማ በሆነ የስራ ቅጥር ዘርፍ (productive employment) እንዳይሰማሩ ባህላዊ ተጽኖኖ ያለባቸው ስለመሆኑና ይልቁንም እንደተለመደው የማይከፈልበት የቤት ውስጥ ስራ ጫና ተሸክመው እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው።

**ደካማ የአባልነት ተሳትፎ:-** ሴቶች በአገር በቀል ድርጅቶች እና የሰራተኛ ማህበራት ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው። ይህም መረጃ የማግኘት ዕድላቸውን እና ችግሮቻቸውን ለመግለጽ መድረኮችን ስለሚገድብ ለተለያዩ ጥቃቶች ተጋላጭነታቸውን በመጨመር እና ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ለማጎልበት እንቅፋት ይሆናል።

**ውሳኔ መስጠት ላይ እኩል ተሳታፊ አለመሆን:-** የተወሰኑ ሴቶች በንብረት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን በጋራ መስጠት ላይ ቢሳተፉም፣ አብዛኞቹ ግን ቁልፍ በሆኑ የኢኮኖሚ ሀብቶች እና ውሳኔዎች ላይ በተለይም ወንድ አባወራ በሆነባቸው ቤተሰቦች ውስጥ በንበረታቸው ላይ የመወሰን ሚና ዝቅተኛ ነው። ይህ ማለት የሴቶች የንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት እንኳን ኑሯቸው ንበረታቸው ላይ የማዘዝ መብት አይኖራቸውም ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሴቶች በኢኮኖሚያዊ ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በሌላውም ጉዳዮች ላይ አቅም እነዳይኖራቸውያደርጋል።

**የግብርና ምርታማነት ማነቆዎች:-** ሴቶች እንደ መስኖና ኤክስቴንሽን የመሳሰሉ አስፈላጊ የግብርና ግብአቶችንና አገልግሎቶችን ለማግኘት ከፍተኛ ተግዳሮቶች ያጋጥሟቸዋል። ይህም በግብርናና ለምግብ ዋስትና ላይ ውጤታማ አስተዋፅዖ እንዳያደርጉ እንቅፋት ስለሚሆኑ ሴት አርሶ አደሮችን ለመደገፍ የታለመ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንደሚያስፈልግ ያመለክታል።

**የሃይልአቅርቦት:-**አንዳንድሴቶችአሁንምለቤትውስጥስራእናምግብለማብሰልየሚጠቀሙትበባዮጋዝነው።ይህምየጤና ችግርእናየአካባቢንዘላቂነት(environmentalsutainability)ስጋትያስከትላል።ይህበባዮጋዝላይጥገኝመሆንእንደአዲስ አበባባሉከተሞችምቢሆንየቀጠለሲሆንይህምየንጹህየሃይልምንጮችንተደራሽነትለማስፋትአስፈላጊመሆኑንያሳያል።

**የኤኮኖሚ ድቀት እና የግጭቶች ተጽእኖ:-** ሴቶች እንደ የምግብ ዋጋ ንረት፣ የግብአት ዋጋ እና ግጭት ባሉ ኢኮኖሚያዊ ሳንካዎች ያልተመጣጠነ ተፅዕኖ ይደርስባቸዋል። ፆታን መሰረት ያደረጉ ተጋላጭነቶችን ያባብሳሉ፤ በፆታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶችን ይጨምራሉ፤ የቤተሰብ መቃወስ እና የስነ ልቦና ጉዳትን ያባብሳሉ። ይህም ሴቶች ችግሮችን የመቋቋም እና የመብቃት አቅምን ለማሳደግ ሁሉን አቀፍ የማህበራዊ ጥበቃ እና የድጋፍ ስርአቶችን አስፈላጊነት አጉልቶ ያሳያል።

## ጤና

**በጤና አጠባበቅ ተደራሽነት ላይ ያሉ መልክዓምድራዊ ልዩነቶች:-** በኢትዮጵያውያን ሴቶች መካከል በጤና አጠባበቅ ተደራሽነትላይከክልልክልልከፍተኛልዩነቶችአሉ።እንደሲዳማያሉአንዳንድክልሎችጎልተውየሚታዩተግዳሮቶችገጥሟቸዋል።

**ለጤና አጠባበቅ የሚውል ገንዘብ እጦት:-** ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ኢትዮጵያውያን ሴቶች አስፈላጊውን የጤና አገልግሎት እንዳያገኙ የሚከለክላቸው የገንዘብ ችግር ነው። ይህ የገንዘብ ችግርም እማወራዎች በሚያስተዳድሯቸው ቤተሰቦች እና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ተባብሶ ይታያል። ይህም ፍትሃዊ የጤና አጠባበቅ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የፋይናንስ አቅምን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ያሳያል።

**የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ማሽቆልቆል:-** በገጠር የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ውጤታማነት ቀንሷል። ይህ የአገልግሎት ጥራት እና ተደራሽነት መቀነስ በሴቶች ጤና ላይ ተጽእኖ እያሳደረ ነው። በተለይ ራቅ ባሉ ክልሎች እና የኤክስቴንሽነ ሰራተኞች የጤና አጠባበቅ መረጃ እና አገልግሎት ዋና ምንጭ በሆኑባቸው አካባቢዎች ችግሩ ተባብሶ ይታያል።

**በጤና እንክብካቤ ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ የተንጸባረቀው መድልዎ እና ማግለል:-** ኢትዮጵያውያን ሴቶች በጤና አጠባበቅ ተቋማት ውስጥ ብዙ ጊዜ አድልዎ እና መገለል ይደርስባቸዋል። ይህም አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዳይሹ ያደርጋቸዋል። ይህ ስርዓታዊ ችግር በጤና አጠባበቅ ስርዓት ስልጠና እና ፖሊሲዎች ዙርያ የበለጠ አካታች እና ደጋፊ ከባቢያዊ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል ጉልህ መሻሻሎች እንደሚያስፈልግ አጉልቶ ያሳያል።

**በቂ ያልሆነ የስነ-ወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና ትምህርት:-** ሴቶች ስለ ወሲባዊ እና ስነ ተዋልዶ ጤና ያላቸው ግንዛቤ ላይ ልዩነቶች አሉ። እንደ ባህል እና የሃብት ውስንነቶች ያሉ ተግዳሮቶች በተለይም በገጠር አካባቢዎች የከፉ ናቸው።

## ትምህርት

**የሴቶች የማንበብና የመጻፍ ክህሎት ምጣኔ:-** በጥናቱ ከተሳተፉት ሴቶች መካከል 55.1% የሚሆኑት ማንበብና መጻፍ አይችሉም። ይህም ከሌሎች ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት ጋር በንጽጽር ሲታይ ዝቅተኛ ነው። ለምሳሌ፣ እንደ ኬንያ እና ደቡብአፍሪካባሉሀገራትማንበብናመጻፍየሚችሉሴቶችመጠንከ70በመቶበላይነው።ይህምየሚያሳየውሴቶችማንበብና መጻፍየሚያስችላቸውመሰረታዊትምህርትእንዲያገኙፖሊሲናፕሮግራሞችንመንደፍእናመተግበርእንደሚያስፈልግነው።

**በየእድሜ ክልል ያለው ሁኔታ:-** የሴቶች የማንበብና የመጻፍ ችሎት እንደየእድሜ ክልል ይለያያል። ወጣት ሴቶች፣ በተለይም ከ15-29 ዓመት የሆናቸው፣ ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ። ነገር ግን በዕድሜ የገፉ ሴቶች፣ በተለይም 50 እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ብዙዎቹ ማንበብና መጻፍ አይችሉም።

**የማህበራዊ እና ክልላዊ ሁኔታዎች ተጽእኖ:-** የኢትዮጵያ ሴቶች በትምህርት የመግፋት ሁኔታ እንደየማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ እና የሚገኙበት ክልል ሁኔት ይለያያል።

**በከተማና ገጠር ያለው ሁኔታ:-** በትምህርት ዘርፍም በከተማና በገጠር መካከል ጉልህ ልዩነት አለ። በከተማ ያሉ ሴቶች ከገጠር ይልቅ የተሻለ የትምህርት ደረጃ አላቸው። በተጨማሪም፣ በከተማም ይሁን በገጠር ሴቶች እንዳይማሩ የሚያደርጉ የተለያዩ እና ውስብስብ መሰናክሎች ያጋጥሟቸዋል የሚያጋጥሟቸው ሲሆን እነዚህ ችግሮችም በገጠር የከፉ ናቸው። እነዚህም ኢኮኖሚያዊ ችግሮች፣ የቤት ውስጥ ስራ፣ ያለ እቻ ጋብቻ እና የአካል ጉዳተኛ ሴቶች የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ናቸው።

# 3.1 ተግዳሮቶች እና ተግዳሮቶችን የመቋቋም አቅም

## ወሲባዊ እና ጾታዊ ጥቃቶች

በሴቶች ላይ የሚደርሰው ጥቃት በተለያዩ የእድሜ ክልል ውስጥ ይለያያል። እንደሚታሰበው ከፍተኛ የጥቃት መጠን የሚታየው በወጣት ሴቶች ላይ ነው። በመቀጠልም፣ የታጩ፣ ከአንድ በላይ ሚስት ያላቸውን ወንዶች ያገቡ (polygamous marriage)፣ በጋብቻ ውስጥ ሁነው ግን በፍርድ ቤት ትዕዛዝም ሆነ በሌላ ምክንያተ ከባላቸው ጋር ተለያይተው የሚኖሩ (separated) ቀጠዩን ከፍተኛውን የጥቃት መጠን ድርሻ ይወስዳሉ። በክልል ደረጃ ልዩነቶች የታዩ ሲሆን በሲዳማ፣ በአፋር እና በጋምቤላ ክልሎች በሴቶች ላይ የሚደርሰው ጥቃት ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም ዝቅተኛ ሀብት ያላቸው ሴቶች እና በገጠር የሚኖሩ ሴቶች ከፍ ያለ የጥቃት መጠን ያጋጥማቸዋል፤ ይህም የድህነትንና እና የተጋላጭነትን ግንኙነት ያሳያል።

በአጠቃላይ በጥናቱ ከተሳተፉት ሴቶች መካከል 20.2% ጥቃት ደርሶባቸዋል። ይህ ቁጥር እንደያውም ትክክለኛውን ምስል ላያሳይ ይችላል። ምክንያቱም ሴቶች የደረሰባቸውን ጥቃት በግልጽነት ለመናገር ስለማይፈልጉ አሊያም ደግሞ አንድ እኪኖሚያዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጥቃቶችን (economic and psychological/ emotional absues) እንደ ጥቃት ስለማይቆጥሯቸው ነው። በተጨማሪም ተፈናቃዮች ባሉባቸው መጠለያ ካምፖች ውስጥ ያሉ ሴቶች እና ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ያሉ ሴቶች ሁሉም አይነት ጾታዊ ጥቃቶች የተጋለጡ ናቸው።

## ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች

**እራስን ስለመተማመን:-** ጥናቱ እንደሚያሳየው ሴቶች በራስ አቅም በመተማን ረገድ አወንታዊ አመለካከት አላቸው። ቢሆንም አሁንም ድረስ የባህላዊ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች፣ የትምህርት እና የኢኮኖሚ ዕድሎች ውስንነት፣ እና ህብረተሰቡ ሴቶች ሊወጡት የሚገባቸውን ሚና አስመለክቶ ያለው አመለካት ተጽእኖ ያሳድሮባቸዋል። በዚህም የተነሳ አሁንም ጥቂት የማይባሉ ሴቶች በራስ የመተማመን ስሜት እና ውሳኔ የመስጠት እድል ይጎድላቸዋል።

**የህይወት እርካታ:-** በርካታ ኢትዮጵያውያን ሴቶች አሁን ባሉበት የኑሮ ሁኔታ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ዝቅተኛ የህይወት እርካታ እንዳላቸው ጠቁመው ከፋይናንስ መረጋጋት፣ ከጤና አጠባበቅ ተደራሽነት፣ ከግጭት አውድ እና ከመሳሰሉት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተግዳሮቶችን እንደምክንያት ጠቅሰዋል። እነዚህ ምክንያቶች የእርካታ ስሜት እነዳይሰማቸው ያደርጋሉ፤ የሴቶችን አጠቃላይ ደህንነትን ስሜት ይጎዳሉ፣ ሴቶች ውጥረት እና ጭንቀትን እንዲጋፈጡ ያርጋሉ።

**ደህንነት እና በራስ መተማመን:-** የኢትዮጵያ ሴቶች በባህላዊ/ማህበራዊ ተጽኖዎች ምክንያት በአብዛኛው ለራሳቸው ዝቅተኛ ግምት ይሰጣሉ፤ ከበታችነት ስሜት ይታገላሉ። ሴቶች በደህንነታቸው እና በራስ የመተማመን ስሜታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ አድልዎ፣ ጥቃት እና መገለል እንደሚገጠማቸው ተናግረዋል።

ምኞቶች እና ሴቶች ላራሳቸው ያላቸው ውክልና

## ምኞቶች እና ሴቶች ላራሳቸው ያላቸው ውክልና

**ሰላምና ደህንነትን በተመለከተ ስለወደፊት ያላቸው ሃሳብ (prospects of peace and security)፡** - በኢትዮጵያ ያሉ ሴቶች ስለወደፊቱ የሰላምና ደህነንት ሁኔታ ሲያስቡ ከፍተኛ ስጋት ይሰማቸዋል፡፡ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ሴቶች ደህንነታቸው ወደፊት በአጭር ጊዜ ውስጥ እየተባባሰ እንደሚሄድ ገምተዋል፡፡

**በአስተዳደር መዋቅር ውስጥ የመሳተፍ ምኞቶች፡-** አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ሴቶች በአካባቢያዊ የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ የመሰማራት ምኞታቸው ዝቅተኛ ለዚህም ሥርዓታዊ እንቅፋቶችን (systemic challenges)፣ እንደ የትምህርት፣ የግብዓት እጥረት እና አሉታዊ ባህሎችን እንቅፋት እንደሆኑ ጠቅሰዋል፡፡

**ዋና ዋና ጉዳዮች ለኢትዮጵያውያን ሴቶች ፡-** ሰላምና ደህንነት ለኢትዮጵያዊያን ሴቶች የቅድሚያ ቅደሚያ አስፈላጊ ጉዳዮች እንደሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልጽዋል፡፡ በተጨማሪም የኤኮኖሚ እድሎች እጦት እና የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ማነስ የኢትዮጵያ ሴቶች አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## ፖለቲካ እና የሲቪክ ተሳትፎ

**የፖለቲካ ግንዛቤ እና አመለካከት፡-**አብዛኛው የኢትዮጵያ ሴቶች በፖለቲካው ውስጥ ምን እየተካሄደ እንዳለ እንኳን መረዳት እንደማይችሉ ይሰማቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በፖለቲካው ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በመሰረቱ ትምህርት ፖለቲካን ለመረዳት እና ለመሳተፍ ወሳኝ መሳሪያ ነው፡፡ ሴቶ በትምህርት ደረጃጀቸው ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር ፖለቲካን ለመገነዝ፣ ለመሳተፍ እና ስልጣን ለመጋራት እና ውሳኔ ለመስጠት ያላቸውን አቅም እያሳዳጉ ይሄዳሉ፡፡ ከላይ እነደተገለጸው የኢትዮጵያ ሴቶች ግን መሰረታዊ የሆነ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ያላቸው እንኳን ከአጠቃላዩ ግምሽ ያህሉ ብቻ ናቸው፡፡

**ስለፖሊሲዎች እና ህጎች ያላቸው ግንዛቤ፡-** ቁልፍ ህጎች እና ፖሊሲዎችን በሚመለከት በኢትዮጵያ ሴቶች መካከል የተለያየ የግንዛቤ ደረጃ አለ፣ በእድሜ ክልል ውስጥ ጉልህ ልዩነቶች አሉ፡፡

## ሰላም እና ደህንነት

**ግጭትን በማስቆም እና በሠላም ግንባታ ሂደት ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ፡-** በኢትዮጵያ የሰላምና የጸጥታ ሂደት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ እጅግ በጣም አናሳ ነው፡፡ ምንም እንኳን ሴቶች በግጭት መከላከል/ ከግጭት በፊት፣ ሽምግልና እና ከግጭት በኋላ መልሶ ግንባታ ላይ የሚጫወቱት ወሳኝ ሚና ቢኖርም በእነዚህ ጉዳዮች ውስጥ በተጨባጭ እንዳይሳተፉ የተገለሉ ናቸው፡፡ ይህ የሥርዓተ-ፆታ አለመመጣጠን ጥልቅ የሆነ የህብረተሰቡን ኢ-እኩልነት እና የአባዊ ስርዓቶችን መንስራፋት የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

**ከክልል ክልል ያሉ ልዮነቶች፡-** ሴቶች ስለ ደኅንነት ያላቸው ግንዛቤ ከክልል ክልል በጉልህ ይለያያል፡፡ እንደ አፋር እና ሀረሪ ባሉ ክልሎች ያሉ ሴቶች በግጭት ውስጥ ካሉ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና አማራ ክልል ውስጥ ካሉት ጋር ሲነፃፀሩ የበለጠ ደህንነት ስሜት ይሰማቸዋል፡፡

**የትጥቅ ግጭቶች አሉታዊ ተጽእኖ፡-** በተለይም እንደ አማራ፣ ትግራይ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ባሉ ክልሎች የትጥቅ ግጭቶች አሳሳቢ ናቸው፡፡ እነዚህ ግጭቶች በሴቶች ደኅንነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፣ ወደ ከፍተኛ ፍርሃት፣ መፈናቀል እና የማህበራዊ ሥርዓት መፈራረስ ይመራሉ፡፡ ስለሆነም አስቸኳይ የግጭት አፈታት እና የሰላም ግንባታ ጥረቶችን ይጠይቃሉ፡፡

**በስርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት እና መዋቅራዊ መሰናክሎች፡-** ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት (GBV) ጉልህ ችግር ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ሌሎች ከመዋቅራዊ እንቅፋቶች ጋር በተየያዘም እንደ የስራ እድሎች እጦት፣ የትምህርት እና የጤና አጠባበቅ ተደራሽነት ውስንነት ከደህንንት ጋር የሚያያዙ አሳሰቢ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ስለሆነም አነዚህን ችግሮች ለመፍታት የፖሊሲም የሆነ የተግባር እርምጃ አስፈላጊ ነው፡፡

**ስለ ሰላም ጉዳይ የተሰጡ የተለያዩ አመለካከቶች፡-** አብዛኞቹ ሴቶች አካባቢያቸውን ሰላማዊ ነው ብለው ሲገልጹ፣ ሌሎች ግን በአካባቢያቸው ያለው የሰላም ሁኔታው እያሽቆለቆለ እንደሆነ ወይም ምንም ሰላም እንደሌለ ይሰማቸዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሰላም እጦት ችግሩ የከፋ ነው ያሉ ሴቶች ባሉባቸው አካባቢዎች ትኩረት ሰጥቶ ችግሩን መፍታት እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡

## 3.2 ምክረ-ሃሳቦች

## ኢኮኖሚያዊ አቅም እና መተዳደሪያን በተመለከተ

### ለመንግስት የተሰጠ ምክረ-ሃሳብ፡

**ሀ/ ሴቶችን ትኩረት ያደረገ ድጋፍ መስጠት፡-** በተለያዩ ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎች እና የስነ-ሕዝብ መገለጫዎች (demographic characteristcs) ያሉ ሴቶችን ነባራዊ ሁኔታ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

**ለ/ ተጨባጭ እርምጃ፡-** ሴቶች የንብረት ባለቤትነት መብት አላቸው ማለት የመወሰን አቅም (decision making power) አላቸው ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም፣,የሴቶችን የንብረት ባለቤትነት መረጋገጥ ብቻ ሳይሆን በንብረታቸው ላይ የመወሰን አቅም እንዲኖራቸው መስራት ያስፈልጋል፡፡

**ሐ/ የመሬት ባለቤትነት መብትን ማጠናከር፡-** የአስር ዓመቱ ሀገራዊ ልማት እቅድ (2021-2030) ስትራቴጂክ ምሰሶ 8 (ሥርዓተ-ፆታ እና ማህበራዊ ማካተት) መሰረት፡ (1) የሴቶችን የንብረት ተጠቃሚነት (መሬት እና መኖሪያ ቤት) የሚደግፉ የቁጥጥር ማዕቀፎችን ማጠናከር ለዚህም የሴቶችን ፍትሃዊ የንብረት ባለቤትነት መብት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን መተግበር; (2) የመሬት/የቤት ባለቤትነት/ባለመብትነትን ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጥረቶችን ማስፋት እና ማጠናከር እንዲሁም በእነዚህ ሰነዶች ላይ መብት እስካላቸው ድረስ የሴቶችን ስም አካቶ ማዘጋጀት፣ በተለይም በአባወራ ቤተሰብ ውስጥ፡፡ ይህን ማድረግ ሴቶች በቀላሉ እንዳይታለሉ ያግዛቸዋል፡፡

**መ/ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን ማሻሻል፡-** እንደ የምግብ ዋስትና መርሃ-ግብር (PSNP) እና የከተማ የምግብ ዋስትና መርሃ-ግብር (UPSNP) ያሉ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን በማጎልበት ብዙ የተቸገሩ ሴቶችን ማገዝ እና የባሰ ኢኮኖሚ ችግር ውስጥ ያሉትንም በገንዘብ መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ ሴቶችን የመቋቋም አቅማቸውን ለማጠናከር እና ኑሯቸውን ለማጎልበት የስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓቶችን መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

**ሠ/ ሴቶች የግብዓት አቅርቦት እንዲያገኙ ማድረግ፡-** ለሴቶች የግብዓት አቅርቦትን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የመስኖ፣ የኤክስቴንሽን ፕሮግራም እና ከቴክኖሎጂ ጋር የተገናኙ መረጃዎች ከአየር ንብረት ጋር የተያያዙ አደጋ ተጋላጭነታቸውን ለመቀነስ ወዘተ፡፡

**ረ/ የሴቶችን የስራ ፈጠራ ክህሎት ማሳደግ፡-** የሴቶችን የፋይናነስ አካታችንት ማሳደግ የግድ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ የቁጠባ ሂሳብ እና ማይክሮ ፋይናንስ፣ የኢንሹራንስ ፖሊሲ እና የፋይናንስ አስተዳደር ክህሎቶቻቸውን ለማሳደግ እና የሴቶችን የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚነት ለማሻሻል መስራት ያስፈልጋል፡፡ የስልጠና፣ የማማከር እና የገንዘብ ድጋፍ እድሎችን ጨምሮ ሴት ስራ ፈጣሪዎችን ለመደገፍ ፕሮግራሞችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ ሴቶች ንግድ መጀመር እና ማሳደግ የሚያስችላቸውን እድል መፍጠር እና ሴቶችን ከስራ እድሎች ጋር ማገናኘት ለታዳጊ ክልሎች እና የገጠር አካባቢዎች ደግሞ ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**ሰ/ የፋይናንስ ደንቦች ለሴቶቶች ፍላጎቶች የተመቹ እንዲሆኑ ማድረግ፡-** የፋይናንስ ደንቦች እና ህጎች ለሴቶች ፍላጎት ምላሽ የሚሰጡ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች የለዩ ለምሳሌ እንደ ብድር ያሉ የገንዘብ ሀብቶችን እንዲያገኙ የሚያግዙ፣ የማስፈጸሚያ ዘዴዎች ያሏቸው፣ ባጠቃላይ እነዚህ ደንቦች የሴቶችን የውሳኔ አሰጣጥ አቅም እና ዕድል ለማሻሻል የሚያግዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

**ሸ/ የሴቶን ትምህርት ማሳደግ፡-** የሴቶችን የትምህርት እና የጎልማሶች ትምህርት ተደራሽነት ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ትምህርት ለሁሉም ነገር ቁልፍ እንደመሆኑ ለምሳሌ ሴቶች ለራሳቸው ያላቸውን ውክልና ለማሳደግ (agency) እና የሥራ ዕድል ተጠቃሚነት ለማሳደግ ትምህርት አስፈላጊ ነው፡፡

**ቀ/ አማራጭ የሃይል አቅርቦት ለሴቶች፡-** ባዮጋዝን ለመብራት አገልግሎትም ሆነ ምግብ ለማብሰል መጠቀም ለሴቶች የጤና ጠንቅ ብቻ ሳይሆን አካባቢንም ይበክላል፡፡ ስለሆነም አማራጭ የሃይል አቅርቦት እና አስፈላጊው የቴክኒክ ስልጠና ድጋፍ ማጠናከር ያስልጋል፡፡

**በ/ የሴቶችን ጥረት የሚደግፉ ፖሊሲዎችን እና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፡-** ለምሳሌ በስራ ላይ የነበረው ፖሊሲና አሁን ለማርቀቅ በሂደት ያለው የሴቶች የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እና ሴቶችን የማብቃትን (women empowerment) ፖሊሲ ማፅደቁ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የአሰሪና ሰራተኛ ህጎች የስርዓ-ጾታ እኩልንትን የሚያሰፍኑ ሴቶች በስራ ገበያው ውስጥ ሙሉ በሙሉ እና በፍትሃዊነት እንዲሳተፉ ማድረግ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ ባሉ ፖሊሲ-እና ውሳኔ ሰጪዎች መካከል ለሥርዓተ-ፆታ መሰረት ያደረገ የበጀት አወጣጥ እና ትግበራን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ሴቶች በአመራች የስራ ዘርፍ (productive employment) ይበልጥ እንዲሳተፉ ለማስቻል አሰሪዎች በአስር አመት የልማት እቅድ ስትራቴጂክ ምሰሶ 9 ላይ በተመለከተው መሰረት ለሰራተኞቻቸው የህጻናት መዋያ መስራት ያስፈልጋል፡፡

## መንግሥታዊ ላልሆኑ እና የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የተሰጠ ምክር-ሃሳብ፡

**ሀ/ ለሴቶች መብት ስለመሟገት፡ (advocate for women's rights)-** መንግስታዊ ያልሆኑ እና የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ከሴቶች መሰረታዊ ድርጅቶች (grassroots organizations) ጋር በመተባበር የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እና የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት የሚያበረታቱ ፖሊሲዎችን እና ህጎች እንዲወጡ እና እንዲተገበሩ ቢሟገቱ ውጤት ሊያመጡ ይችላሉ። እንዲሁም፣ ሴቶች በገቢ ማስገኛ ተግባራት ውስጥም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ሴቶች ስለሚኖራቸው ሚና ህበረተሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመለወጥ ግንዛቤ መፍጠር እና ማሳደግ ላይ ቢሰሩ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ።

**ለ/ አቅም ግንባታ ፡-** መንግስታዊ ያልሆኑ እና የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ሴቶች የኢኮኖሚ እድሎቻቸውን እና አቅምን ለማሳደግ በስራ ፈጠራ፣ በፋይናንሺያል አስተዳደር እና በአመራር ክህሎት ላይ ስልጠና እና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን አጠናክረው ለቀጥሉ ይገባል። አዲስ በታወጀው የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ (2024) መሰረት ሴቶች የመሬት ይዞታ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

## ለልማት አጋሮች፡ የተሰጠ ምክረ-ሃሳብ

**ሀ/ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን እና የኢኮኖሚ ልማትን መደገፍ:-** የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ መብቶች እና እድሎች የሚያበረታቱ ፖሊሲዎችን ለማውጣት እና ተግባራዊ ለማድረግ በተለይም የሴቶችን የመሬት መብት የሚያበረታቱ ፕሮጀክቶችን፣ የፋይናንስ አካታችነት እና የኢኮኖሚ አቅምን ለማጎልበት የቴክኒክ ድጋፍ እና የገንዘብ ድጋፍን ቢያሳድጉ መልካም ነው።

**ለ/ አጋርነትን ማጎልበት፡-** በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች የሴቶችን ልዩ ፍላጎትና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የስርዓተ-ፆታ ምላሽ ፕሮግራሞችን እና ተጨባጭ እንቅስቃሴዎችን (interventions) ተግባራዊ ለማድረግ ከሀገር ውስጥ ድርጅቶች እና የመንግስት ኤጀንሲዎች ጋር ቢተባበሩ መልካም ነው።

# ጤናን በተመለከተ የተሰጡ ምክረ-ሃሳቦች

## ለመንግስት

**ሀ/ የጤና አጠባበቅ ተደራሽነትን ማሻሻል:-** የሴቶችን የጤና አገልግሎት ለማሻሻል የጤና አጠባበቅ መሠረተ ልማቶችን ማሻሻል ከመንግስት የሚጠበቅ ነው። በተለይም በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች እንዲሆም በገጠር አካባቢዎች የሴቶችን የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ተደራሽነት ለማሳደግ ብርቱ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ለምሳሌ፣ በተለይም በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች የተሻለ የጤና መድህን እጥረት እና የትራንስፖርት ችግሮችና መሰናክሎችን መፍታት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው።

**ለ/ የፆታዊ እና የስነ ተዋልዶ ጤና ትምህርትን ማጠናከር፡-** ሴቶች ስለ ስነ ተዋልዶ ጤንነታቸው በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲወስኑ በትምህርት ቤቶች፣ በመህበረሰብ ዘንድ እና በጤና አጠባበቅ ተቋማት ሁሉን አቀፍ የስነ-ወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና ትምህርት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

**ሐ/ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ማሻሻል፡-** የወሊድ መከላከያ እና የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን ጨምሮ የተለያዩ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎችን በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም፣ ስለቤተሰብ ዕቅድ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እና በአጠቃቀም ላይ ያሉ የባህል እንቅፋቶችን ለመፍታት የታለሙ ዘመቻዎች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይም የእናቶች እና ህፃናት ጤና (MCH) እና የስነ-ወሲብና ስነ-ተዋልዶ ጠየና (SRH) አገልግሎቶች ልዩ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል።

**መ/ የወር አበባ ጤና ፍላጎቶችን ማሟላት፡-** በተመጣጣኝ ዋጋ ጥራት ያላቸውን የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ ምርቶችን ተደራሽነትን ለማሻሻል ውጥኖችን ማዘጋጀት እና ስለ የወር አበባ ንፅህና አጠባበቅ ለሴቶች ትምህርት መስጠት፣ ስላሉት አማራጮች እና ትክክለኛ አወጋገድ ዘዴዎችን ጨምሮ ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል።

## መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ድርጅቶች

**ሀ/ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና ትምህርት ፕሮግራሞችን ማካሄድ:-** መንግስታዊ ያልሆኑ እና የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ከማህበረሰብ ጋር በመተባበር በጾታዊ እና ስነ ተዋልዶ ጤና፣ በቤተሰብ ምጣኔ እና በወር አበባ ንፅህና አያያዝ ላይ ያተኮሩ የጤና ትምህርት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ቢያደርጉ መልካም ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ ፕግራሞች የአካባቢውን ባህል ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገቡ፣ የአካባቢውን ባህል የሚያከብሩ መሆን ይኖርባቸዋል።

**ለ/ ለፖሊሲ ለውጥ ማቀንቀን፡-** መንግሳታዊ ያልሆኑ እና የሲቪክ ድርጅቶች ለሴቶች ጤና ቅድሚያ የሚሰጡ ፖሊሲዎች እንዲፀድቁ እና እንዲተገበሩ ማቀንቀን ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ፣ የጤና አጠባበቅ ተደራሽነትን እንቅፋቶች ለመፍታት፣ የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል እና ተመጣጣኝ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ምርቶችን ሴቶች ማግኘት እንዲችሉ ማቀንቀን ይችላሉ።

**ሐ/ የድጋፍ አገልግሎት መስጠት፡-** በመላው ኢትዮጵያ ያሉ ሴቶችን ልዩ ልዩ ፍላጎቶች ለመፍታት የምክር፣ የስነ ተዋልዶ ጤና ክሊኒኮች እና የማህበረሰብ አቀፍ የጤና አጠባበቅ ውጥኖችን ጨምሮ ለሴቶች ጤና የድጋፍ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ።

## ዓለም አቀፍ አጋሮች

**ሀ/ የጤና መሠረተ ልማት ልማትን መደገፍ፡-** ዓለም አቀፍ አጋር አካላት ለኢትዮጵያ መንግሥት የጤና አጠባበቅ መሠረተ ልማቶችን ለማጠናከር እና ለሴቶች በተለይም በገጠርና ራቅ ባሉ አካባቢዎች ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሻሻል የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

**ለ/ ለሥነ ተዋልዶ ጤና ፕሮግራሞች የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፡-** እነዚህ አለም አቀፍ አጋር አካላት የሥነ ተዋልዶ ጤና መርሃ ግብሮች ለማስፈጸም፣ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ለማስፈት፣ ለእናቶችን ጤና አጠባበቅ፣ የሴቶች እና ሴት ልጆችን የጾታዊ-ግንኙነት እና ሥነ ተዋልዶ ጤና ትምህርት ተደራሽነትን ለማሻሻል ዓላማ ያላቸውን ድጋፎች አጠናክረው መቀጠል ቢችሉ ጥሩ ነው።

**ሐ/ በየአካባቢው ካሉ አደረጃጀቶች ጋር በአጋርነት መስራት፡-** የሴቶችን የጤና ፕሮግራሞችን እና ትግበራዎችን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በየአካባቢው ካሉ ድርጅቶች እና የመንግስት ኤጀንሲዎች በትብብር ቢሰሩ መልካም ነው።

# ትምህርትን በተመለከተ

## ለመንግስት የተሰጠ ምክረ-ሃሳብ፡

**ሀ/ የትምህርት ተደራሽነትን ማሳደግ፡-** በተለይም እድሚያቸው ከ30 ዓመት በላይ የሆኑ በተለይም በገጠር እና ብዙ አገልግሎት በሌለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የሴቶች እና ሴት ልጆች ትምህርት ተደራሽነትን (ለምሳሌ የጎልማሶች ትምህርት) ማሳደግ ከመንግስት ይጠበቃል። በተጨማሪም በጦርነት የተጎዱትን የትምህርት ተቋማት መልሶ መገንበት እና የማንበብና መጻፍ ክህሎትን (literacy) እንዲያደብሩ ለሴቶች ፍትሃዊ የትምህርት ተደራሽነትን ማረጋገጥ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። ይህንን ችግር ይበልጥ ለመቅረፍ በዝቅተኛ የኢኮኖሚ አቅም ውስጥ ያሉትንም ሴቶች ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

**ለ/ ትምህርት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን መፍታት፡-** ሴቶች እና ሴት ልጆች በትምህርት ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን እንቅፋቶች ለመቅረፍ ውጥኖችን ማዘጋጀት፣ ለሴቶች ትምህርት ቤተሰብ ድጋፍ እንዲያደርግ ግንዛቤ ማስጠት፣ ፣ የገንዘብ ችግር ማቃለል፣ ለማይከፈልባቸውን የቤት ውስጥ ስራዎች ጫና መቀነስ፣ ሴት ልጆች ወደትምህርት ቤት እንዲሄዱ እና እንዳያቋርጡ የሚያበረታቱ ስልቶችን ሁሉ መተለም እና መተግበር ያስፈልጋል።

**ሐ/ ሴቶች የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና አጠቃቀሙንም እንዲያውቁ ማድረግ፡-** ሴቶች እና ሴት ልጆች ቴክኖሎጂን የመጠቀም ክህሎት እንዲኖራቸው ለማድረግ የዲጂታል ማንበብና መጻፍ (digital literacy) ፕሮግራሞችን ወደ ትምህርት ስርአተ ትምህርት ማካተት ያስፈልጋል። በትምህርት ቤቶች እና ማህበረሰብ ውስጥ የኮምፒተር እና የኢንተርኔት ግብአቶችን ማቅረብ ያስፈልጋል።

## መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማኅበራት

ሀ/ **ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ፖሊሲዎች መውጣት እና መተግበር ማቀንቀን፡-** መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማህበራት የሴቶችና ሴት ልጆችን እኩል የትምህርት ተደራሽነትን የሚያበረታቱ የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ ፖሊሲዎችን እና ህጎች እንዲወጡ፣ እንዲጸድቁ እና እንዲተገበሩ መደገፍ ይጠበቅባቸዋል። ስለ ሴት ልጆች ትምህርት አስፈላጊነት እና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት በትምህርት ውስጥ ስላለው ጥቅም ግንዛቤን ማሳደግ ስራም መስራት ቢችሉ መልካም ይሆናል።

ለ/ **የትምህርት ድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት፡-** መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሲቪክ ማህበራት ሴቶች እና ሴት ልጆች በትምህርት ረገድ የሚገጥማቸውን መሰናክሎች እንዲያልፉ እና የአካዳሚክ ስኬት እንዲያመጡ ለማስቻል የትምህርት ድጋፍ አገልግሎቶችን ማለትም እንደ ስኮላርሺፕ፣ የምክር ፕሮግራሞች እና የማስተማር አገልግሎት መስጠት ይችላሉ።

ሐ/ **የማህበረሰብ ተሳትፎን ማሳደግ፡-** የሴቶች እና የሴት ልጆችን ትምህርት ጠቀሜታ ለማስተዋወቅ፣ አድሏዊ የሆኑ የስርዓተ-ፆታ ደንቦችን እና አመለካከቶችን ለመቃወም እና ለሴት ልጆች ትምህርት ድጋፍ እንዲደረግ የማህበረሰብ ግንዛቤን እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን ማካሄድ ያስፈልጋል።

## አለምአቀፍ አጋሮች

ሀ/ **የትምህርት ልማትን መደገፍ፡-** በኢትዮጵያ የሴቶች እና የሴት ልጆች የትምህርት ጥራት ተደራሽነትን ለማሻሻል የታለሙ የትምህርት ልማት እቅዶችን የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የገጠር ሴት ልጆች፣ አካል ጉዳተኛ ሴት ልጆች እና አናሳ ማህበረሰብ ክፍሎችን ትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋፋት የሚታቀዱ እቅዶችን እና ትግበራዎችን በገንዘብ መደገፍ ከአለም አቀፍ አጋር አካላት ይጠበቃል።

ለ/ **በትምህርት ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ማሳደግ፡-** የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እና የሴቶችን የማብቃት መርሆችን ከትምህርት መርሃ ግብሮች እና ፖሊሲዎች ጋር በማቀናጀት በትምህርት ተደራሽነት፣ ማቆየት እና ማጠናቀቂያ ደረጃዎች ላይ የስርዓተ-ፆታ ልዩነቶችን በማስወገድ ላይ አተኩረው መስረት ይጠበቅባቸዋል።

ሐ/ **በአቅም ግንባታ ላይ ተባብሮ መሥራት፡-** ሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ እና አካታች የትምህርት ተግባራትን ለማረጋገጥ የመምህራን ሥልጠና፣ ሥርዓተ ትምህርት፣ ክትትልና ግምገማን ጨምሮ በትምህርት ሥርዓቶችና ተቋማት ውስጥ አቅምን ለማጎልበት ከአገር ውስጥ ድርጅቶችና የመንግሥት ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር ቢሰሩ መልካም ነው።

# ወሲባዊና ፆታ ተኮር ጥቃት እና ደህንነትን በተመለከተ

## መንግስት

ሀ/ **የፍትህ ተደራሽነትን ማሳደግ፡-** ልዩ ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም፣ ለህግ አስከባሪ አካላት እና ለህግ ባለሙያዎች በስርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ላይ ስልጠና በመስጠት የፍትህ ስርዓቱ ለወሲባዊና ፆታ ተኮር ጥቃት ጉዳዮች የሚሰጠውን ምላሽ ማሳደግ እና ተጎጂዎች የህግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ መንግስት መስራት ይጠበቅበታል። የድህረ-ግጭት የፍትህ ስርዓትን ማጠናከር፣ የጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ፍትህ እንዲያገኙ ሰጣቸው ማድረግ፣ የህግ ሂደቶችን ቀልጣፋ ማድረግ እና የህግ አስከባሪ አካላትን ጥረት ውጤታማ ማድረግ የመንግስት ሃላፊነት ነው። ይህ ለፍትህ አካላት ሠራተኞች ልዩ ሥልጠና መስጠትን፣ እነዚህ አካላት ለተጎጂዎች ቀልጣፋ ፍትህ እንዲያገኙ ማድረግ እና ለዚህም ልዩ ችሎቶችን የአንድ መስኮት አገልግሎትን ማደራጀት፡ ሽፋኑን ማስፋትና እና ሌሎች አገልግሎቶችንም ባካተተ መልኩ።

ለ/ **የመከላከያ /የጥብቃ ፕሮግራሞችን መተግበር፡-** የጾታዊ ጥቃት ዋና መንስኤዎችን የሚፈቱ፣ ጎጂ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን እና አመለካከቶችን የሚቀንሱ እና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን እና መከባበር እና እኩልነት ላይ የተመሰረቱ የስርዓተ-ጾታ ግንኙነቶችን ማስፈን ከመንግስት ይጠበቃል።

ሐ/ **የድጋፍ አገልግሎቶችን ማስፋፋት፡-** ከፆት ተኮር ጥቃት በሕይወት ለተረፉ ሰዎች የድጋፍ አገልግሎቶችን የገንዘብ ድጋፎችን እና ግብዓቶችን ማሳደግ፣ መጠለያዎች፣ የስልክ መስመሮች፣ የምክር አገልግሎት እና የህክምና እና የስነ-ልቦና-ማህበራዊ ድጋፍን ጨምሮ መስጠት ያስፈላጋል።



## መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማህበራት

ሀ/ **ግንዛቤ ማሳደግ፡-** ስለ GBV ስርጭት እና መዘዝ ህብረተሰቡን ለማስተማር፣ ተጎጂዎችን እርዳታ እንዲፈልጉ ለማበረታታት፣ እና ህብረተሰቡ ጥቃትን ለመከላከል እርምጃ እንዲወስድ በማስተባበር የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን ማካሄድ ከመንግስታዊ ድርጅቶች እና ሲቪክ ማህበራት ይጠበቃል።

ለ/ **ድጋፍ ማድረግ እና ስለሴቶች መብቶች መሟገት (advocacy):-** ለተጎጂዎች  የህግ ድጋፍ ማድረግ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታዎችን ጨምሮ የድጋፍ አገልግሎቶችን ማቅረብ፣ እና የተነደፉ ስልቶች የተደነገጉ መብቶችን ተግባረዊ እንዲሆኑም ሆነ ሌሎች የሴቶች መብቶች የሚያረጋግጡ ሌሎች ህግጋት እንዲወጡ እና እንዲፈጸሙ መሟገት መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከሲቪክ ማህበራት ይጠበቃል። በተጨማሪም የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን ተግባራዊ ለማድረግ፣ ወንዶችን ያሳተፈ ጸረ--ጾታዊ ጥቃት ትግል ማድረግ፣ ጎጂ የስርዓተ-ፆታ ደንቦችን እና የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ትምህርት ሥርዓት ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል።

## አለምአቀፍ አጋሮች

ሀ/ **ቴክኒካል እና ፋይናንሺያል ድጋፍ ማቅረብ፡-** ለመንግስት ኤጀንሲዎች፣ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና አገልግሎት ሰጪዎች አቅም ግንባታን ጨምሮ ሀገራዊ የጾታ ጥቃት  ምላሽ ሰጪ ስርዓቶችን ለማጠናከር የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ማቅረብ ቢችሉ መልካም ነው። ይህ ድጋፍም በተፈናቃዮች መጠለያ ካምፕ ውስጥ የሚገኙ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሰለባ  ለሆኑ ተጎጂዎች ጭምር መሆን ይኖርበታል።-

ለ/ **ትብብርን ማሳደግ፡-** በመንግስታት፣ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና በአለም አቀፍ ኤጀንሲዎች መካከል አጋርነትን እና ትብብርን ማጎልበት፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን መለዋወጥ እና ጾታዊ ጥቃት ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ትብብሮችን ማሳዳግ ይጠበቃል።

ሐ/ **ለፖሊሲ ለውጥ መሟገት፡-** ጾታዊ ጥቃትን ለመከላከል እና ምላሽ ቅድሚያ ለመስጠት፣ ለዚሁ አላማ በቂ ሀብት እንዲመደብ፣ እና መንግስት የጾታዊ ጥቃትን እንዲከላከል እና ለተጎጆዎች ፍትህ እንዲሰጥ፣ በሀገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ ደረጃ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ለመደገፍ እና ለመሰል ጉደዮች አለማ አቀፍ አጋር ድርጅቶች በፕሮግራማቸው ማካተቱ ጥሩ ይሆናል። በተጨማሪም አዲስ የወጣውን የሽግግር የፍትህ ፖሊሲ ተግባራዊነት እና ሴቶች ከዚሁ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ ይኖርባቸዋል።

# የስነ-ልቦና ደህንነትን በተመለከተ

## መንግስት

ሀ/ **በአእምሮ ጤና መሠረተ ልማት ላይ መዋዕለ-ነዋይ ማፍሰስ፡-** የአዕምሮ ጤና እንክብካቤ ተቋማትን እና አገልግሎቶችን በተለይም አገልግሎት በሌላቸው ገጠራማ አካባቢዎች ለማስፋፋት ግብዓቶችን ማሟላትና ለሁሉም ሴቶች ተደራሽ እንዲሆን መንግስት መስረት ይጠበቅበታል።

ለ/ **የስነ አእምሮ ጤና ፖሊሲዎችን መተግበር፡-** ለአእምሮ ጤና ግንዛቤ፣ ትምህርት እና ድጋፍ ፕሮግራሞች ቅድሚያ የሚሰጡ ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት እና መተግበር፣ ከነባር የጤና አጠባበቅ ሥርዓቶችም ጋር ማዋሃድ ያስልጋል። የትግራይ፣ የአማራ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ባሉ ክልሎች የስሜት መቃወስ (trauma) ህክምና ላይ ስልጠና እና የምክር አገልግሎት መስጠት ያስፈልጋል።

ሐ/ **ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ውጥረቶችን (stressors) መቅረፍ፡-** በሴቶች አእምሯዊ ደህንነት ላይ የሚኖረውን ጫና ለማቃለል በጥናቱ ውስጥ የተለዩትን እንደ የስራ አጥነት እና የተረጋጋ የገንዘብ ምንጭ አለመኖር ያሉ የተለመዱ ውጥረቶችን የሚፈቱ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን መተግበር ያስልጋል። የተሟላ የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕከላት ማዘጋጀት፣ አስተማማኝ ሪፈራል ትስስር ከአገልግሎቶችን ማመቻቸት፣ ጉዳት የደረሰባቸው ሴቶችን እና ማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳግ የምክር አገልግሎትን ማጠናከር እና ማስፋፋት። (ግለሰብ፡ አቻ ለአቻ፣ የቡድን እና የማህበረሰብ)

## መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማህበራት

**ሀ/ የሰነ አእምሮ ጤና ድጋፍ አገልግሎቶችን ይስጡ፡-** መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማህበራት ሴቶችን ተደራሽ የሚያደርግ እና ለባህል ተስማሚ የሆነ የአእምሮ ጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለመስጠት የምክር፣ የህክምና እና የድጋፍ ቡድኖችን ጨምሮ ማህበረሰቡን መሰረት ያደረጉ የአእምሮ ጤና ድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት ቢችሉ መልካም ነው። መጀመሪያ በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል እና በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች ግጭት ባለባቸው አሊያም ቅርብ ጊዜ ከግጭት በወጡ ማህበረሰቦች ላይ ትኩረት ቢያረጉ መልካም ይሆናል።

**ለ/ ለሴቶች የሰነ አእምሮ ጤና መብቶች መሟገት፡-** ለሴቶች የአእምሮ ጤና መብቶች ቅድሚያ ለሚሰጡ ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች መሟገት፣ በስርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረቱ የመብት ጥሰቶችን ለመቅረፍ እና ለሥርዓተ-ፆታ ተጋላጭ የሆነ የአእምሮ ጤና እንክብካቤን ጨምሮ በሌሎችም ጉዳዮች ዙርያ አሰራር እንዲበጅላቸው እና ተፈጻሚነታቸው እንዲረጋገጥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማህበረሰብ አባልት ቢሟገቱ ውጤት ሊያስመዘግቡ ይችላሉ።

**ሐ/ ግንዛቤን ማሳደግ፡-** በአእምሮ ጤና ጉዳዮች ዙሪያ ያለውን አድልዎ እና ማገለል (stigma) ለመቀነስ እና ሴቶች ድጋፍ እንዲጠይቁ ለማበረታታት የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን እና ትምህርታዊ አውደ ጥናቶችን ማካሄድ ይጠበቅባቸዋል።

## አለምአቀፍ አጋሮች

**ሀ/ የቴክኒክ እና የፋይናንስ ድጋፍ መስጠት፡-** በኢትዮጵያ የአእምሮ ጤና መሠረተ ልማቶችን እና የአቅም ግንባታ ጥረቶችን ለማጠናከር በተለይም በገጠር እና በተገለሉ ማህበረሰቦች እንዲሁም ከጦርነት በማገገም ላይ ባሉ እንደ ትግራይ ያሉ አካባቢዎች የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ቢያደርጉ መልካም ነው።

**ለ/ የአቅም ግንባታ፡-** የሥልጠና ፕሮግራሞችን፣ አውደ ጥናቶችን እና ከሌሎች አገሮች ባለሙያዎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድግን ጨምሮ ለአካባቢው የስነ አእምሮ ጤና ባለሙያዎች የሚሠጡ የአቅም ግንባታ መርሃ ግብሮችን መደገፍ ቢችሉ መልካም ነው።

**ሐ/ ጥናትና መረጃ አሰባሰብ፡-** የኢትዮጵያ ሴቶችን የአእምሮ ጤና ፍላጎት የበለጠ ለመረዳት እና በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ እና ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦችን ለማመንጨት የሚረዱ ስራዎችን እነዚህ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማህበረታ ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ።

# የፍትህ ተደራሽነትን በተመለከተ

## የመንግስት ለመንግስት አካላት

**ሀ/ የግጭት መፍቻ ስርዓቶችን ለሴቶች ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ፡-** የሴቶችን መብቶች በብዛት የሚጎዱ የመሬት፣ የፍቺ እና የንብረት መብቶችን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ በማተኮር የህግ ማዕቀፎችን እና አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚረዱ ዘዴዎችን ማጠናከር ከመንግስት ይጠበቃል።

**ለ/ በገጠር ለሚኖሩ ሴቶች የህግ አግልገሎትን ተደራሽ ማድረግ፡-** በተለይም የገጠር ሴቶች ፍትህን በማግኘት ረገድ ትልቅ ፈተና ስለሚገጥማቸው የህግ አገልግሎቶች እና የህግ ድጋፍ ፕሮግራሞች ተደራሽነትን ማሳደግ ያስፈልጋል። የሴቶችን መብት የሚመለከቱ ጉዳዮችን በብቃት ለማስተናገድ ለህግ ባለሙያዎች እና ለማህበረሰብ አስታራቂዎች የስልጠና እና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ መስራት ከመንግስት ይጠበቃል።

**ሐ/ ሴቶች በጾታ ላይ ተመሰርቶ ለሚደርስባቸው ጥቃቶች ፍትህ እንዲያገኙ ማድረግ፡-** በጾታ ላይ ተመስርቶ ሴቶች የሚደርስባቸውን ጥቃቶች፡ በሴቶች ላይ የሚደርሱ አድልዎ እና ማገለሎችን የሚመለከቱ ልዩ ፍርድ ቤቶችን (specilailzed courts or tribunals) ማቋቋምና ማሰፋፋት ያስፈልጋል። በተጨማሪም መንግስት ቀልጣፋ እና ገለልተኛ የፍትህ ስዓትን ማስፈን ይኖርበታል። በጾታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶችን ለሚመረምሩ የፖሊስ አባላትን አቅም ማጠናከር፣ በጾታ ላይ የተመሰረቱ የመብት ጥሰቶችን ብቻ የሚመረምሩ ችሎቶችን ማቋቋም ያስፈልጋል።







## መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪል ድርጅቶች

**ሀ/ ስለ መብቶቻቸው ግንዛቤ ማስጨበጥ፡-** መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማህበራት ሴቶች ስላላቸው መብቶች እና የህግ መፍትሄዎች ለማሳወቅ የህግ ግንዛቤ እና የትምህርት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድግ፣ የሴቶችን የፍትህ ተደራሽነት የሚያደናቅፉ ማነቆዎችን እና አድሎአዊ ጉዳዮችን ለመፍታት እንደአስፈላጊነቱ የፖሊሲ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ መሟገት፣ የሴቶች መዋቅሮች እና ተጎጂዎች በንቃት እንዲሳተፉ እና ከሽግግር ፍትህ ፖሊሲ እና ከሂደቱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ እነዚህ አካላት መሟገት ይጠበቅባቸዋል።

**ለ/** የሴቶችን ፍላጎትና ጥቅም የሚያስቀድሙ ማህበረሰብ አቀፍ የሽምግልና እና የሙግት አፈታት ዘዴዎችን በማቋቋም በሂደቱ ውስጥ ሴቶች ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## አለምአቀፍ አጋሮች

**ለስርዓ-ጾታ ልዩነቶች ምላሽ የሚሰጥ የፍትህ ስርዓትን ማስፈን፡-** የህግ የበላይነትን ለማጠናከር እና የስርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ የፍትህ ስርአቶችን በኢትዮጵያ ማሳደግ፣ የቴክኒክ ድጋፍ እና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ጨምሮ የሴቶች ፍትህ አገልግሎት የሚያሳድጉ ውጥኖችን ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል። የፍትህ ተደራሽነትን ለማሳደግ ለሴቶች በተለይም በገጠር እና በተገለሉ ማህበረሰቦች አካባቢ የህግ ድጋፍ የሚሰጡ ፕሮጀክቶችን በገንዘብ መደገፍ ከእነዚህ አለም አቀፍ አጋር አካላት ይጠበቃል። የህግ ድጋፍ ፕሮግራሞችን እና የክርክር አፈታት ዘዴዎችን ውጤታማነት ለመከታተል እና ለመገምገም ከአካባቢው ባለድርሻ አካላት ጋር መተባበር፣ መሻሻል ያለባቸውን እንዲሻሻሉ ሃሳብ ማቅረብና መልካም ተሞክሮዎች ደግሞ እንዲሰፉ ማገዝ ከእነዚህ አካላት የሚጠበቅ ነው።

# ፖለቲካ እና የሲቪክ ማህበረሰብ ተሳትፎን በተመለከተ

## ለመንግሥት የተሰጠ ምክረ-ሃሳብ

**ሀ/ ሴቶች በመብቶቻቸው ዙርያ ያላቸውን እውቀት (legal literacy) ማሳዳግ፡-** ሴቶች ስለሕጎች እና ፖሊሲዎች ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ በተለይም እንደ የሠራተኛ ሕግ ባሉ ብዙም ያልታወቁ ጉዳዮች ላይ በማተኮር አጠቃላይ የሕግ ትምህርት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ከአካባቢው ባህል ጋር የሚስመማ (culturally sensitive)፣ ተደራሽ የሆነ ትምህርታዊ ዘመጃወችን ማድረግ ከመንግስት የሚጠበቀቅ ነው።

**ለ/ የሴቶችን የፖለቲካ ውክልና ማሳደግ፡-** በሁሉም የመንግስት እርከኖች የሴቶችን የፖለቲካ አመራር ሚና ለማሳደግ አዎንታዊ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ሴቶች በውሳኔ ሰጪ አካላት ሁነው በፍትሃዊነት ውክልና እንዲኖራቸው በምርጫ ሥርዓት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ኮታ-ስረዓት ቢኖር መልካም ይሆናል።

**ሐ/ የሴቶችን የምርጫ ተሳትፎ ማረጋገጥ፡-** የሴቶችን በምርጫ ተሳትፎ ለማበረታታት እና ለማመቻቸት የምርጫ ሂደቶችን ማጠናከር ያስፈልጋል። የምርጫ ካርድ መዘግየቶች ያሉ የሎጂስቲክስ ተግዳሮቶችን መፍታት እና በምርጫ ጣቢያዎች የሚፈጠሩትን ሁከት ፍራቻዎች ለመከላከል የደህንነት እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል።

## የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች

**ሀ/ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ማጎልበት:-** የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ሴቶች በፖለቲካዊ ሂደቶች ውስጥ በብቃት እንዲሳተፉ ለማድረግ የስልጠና እና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን መተግበር ይችላሉ። በተጨማሪም ሴቶች በፖለቲካ ውስጥ ውጤታማ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የአመራር ስልጠና መስጠት ፣ የተሟጋችነት ክህሎት (advocacy) ክህሎትን ማሳደግ እና የሜንተርሽፕ መርሃ-ግብሮችን ማሳደግ ያስፈልጋል።

**ለ/ የሴቶች መብት ግንዛቤን ማሳደግ:-** የሲቪክ ማህበረሰብ አባላት በኢትዮጵያ ህገ መንግስት እና አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት የተደነገጉ የሴቶች መብቶች ዙርያ ግንዛቤን ለማሳደግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን እና የማህበረሰብ አውደ ጥናቶችን ማካሄድ ይኖርባቸዋል። የሴቶችን ድምጽ ለማጉላት እና የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፋፋት ህዝባዊ ንቅናቄ እና በህበረተሰቡ ዘንድ የሴቶች መብቶች ተሟጋችነትን ለማሳደግ መስረት ይኖርባቸዋል፡፡

**ሐ/ የስነ-ዜጋ ትምህርትን ማጠናከር:-** የሲቪክ ማህበረሰብ አባላት ከመንግስት ኤጀንሲዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በሴቶች መብት፣ በዜግነት ኃላፊነቶች እና በምርጫ ሂደቶች ላይ በማተኮር የስነ-ዜጋ ትምህርት ፕሮግራሞችን ማስፋት ይኖርባቸዋል። ይህም ሲደረግ በፖለቲካ ባህል ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድሩ ወንዶችን ማሳተፍ ያስፈልጋል፡፡

## አለምአቀፍ አጋሮች

**ሀ/ የሴቶችን የፖለቲካ አመራር ሚና መደገፍ:-** የሴቶችን የፖለቲካ አመራር እና ተሳትፎን ለሚያሳድጉ መርሀ-ግብሮች የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ መስጠት ከአለም አቀፍ አጋር አካላት የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። ለሴት መሪዎች፣ ለምርጫ ታዛቢዎች እና ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ስርዓተ-ፆታን ያካተተ አስተዳደርን የሚደግፉ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ማስፋትም ያስፈልጋል።

**ለ/ ለሥርዓተ-ፆታ እኩልነት የሚረዱ ፖሊሲዎች እና ትግባራዎች መሟጋት:-** ለሥርዓተ ፆታ እኩልነት የሚያግዙ ፖሊሲዎችን እና ህጎችን በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲፀድቅ እና እንዲተገበሩ አለመአቀፍ አጋር አካላት መሟገት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ሴቶች በፖለቲካዊ ተቋማት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለማሳደግ እርምጃዎችን መውሰድን ያካትታል፡፡

**ሐ/ የምርጫ ሂደቶችን መከታተል እና መገምገም:-** የምርጫ ሂደቶችን ለመከታተል እና ለመገምገም የሚደረጉ ጥረቶችን አለም አቀፍ አጋር አካላት መደገፍ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህም ስርዓተ-ፆታ ጠቋሚዎች (Indicators) እና በሴቶች ተሳትፎ ላይ በማተኮር መስራት ይቻላል። ለገለልተኛ የምርጫ ታዛቢዎች የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ እና በምርጫ ሥርዓት ውስጥ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን የሚያበረታቱ ጅምሮች መደገፍ ይጠበቅባቸዋል።

# ሰላም እና ደህንነትን በተመለከተ

## ለመንግስታዊ አካላት የተሰጠ ምክር-ሃሳብ

**ሀ/ ሰላምና ደህንነትን የሚያጎለብቱ የመንግስት ተግባራት:-** በግጭት አፈታት ዘዴዎች፣በሰላም ግንባታ ውጥኖች እና በማህበረሰብ የውይይት መድረኮች ሰላምና ደህንነትን ለማስፈን ጥረቶችን ማጠናከር ያስፈልጋል። የግጭት መንስኤዎችን ለመፍታት እና የማህበረሰብ ትስስርን የሚያበረታቱ የግጭት መከላከል እና አፈታት ፕሮግራሞች ላይ መዋዕለ-ነዋይ ማፍሰስ በተለይም ግጭት በተከሰተባቸው ማለትም በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ትግራይ ፣ ጋምቤላ እና አንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። በሁሉም የሰላም ሂደቶች፣ ውይይቶች እና ተነሳሽነት ሴቶችን ተሳታፊ ማድረግ ያስፈለጋል።

**ለ/ ፖሊሲዎችን መተግበር:-** ተጨማሪ የስራ እድሎችን ለመፍጠር እና የትምህርት እና የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሻሻል ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በሴቶች የሚነሱ ቁልፍ ጉዳዮችን ማለትም እንደመሰረተ-ልማት ዝርጋታ ( ለምሳሌ ንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፣መንገዶች እና የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት) እና በተለይም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ የሰላም እና ደህንነትን ችግሮችን መፍታት ያስፈልጋል፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች እና የሴቶችን መብት ለማስጠበቅ የህግ ማሻሻያዎችን ጨምሮ በስርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶችን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት አጠቃላይ ስልቶችን ማዘጋጀትም ያስፈልጋል።

## መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪክ ማህበራት

**የግጭት ሽምግልና እና እርቅ መርሃ-ግብሮችን ጨምሮ ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ የሰላም ግንባታ ውጥኖችን ማመቻቸት:-** መሬት ላይ ያሉ ውጥረቶችን ለመፍታት እና ማህበራዊ ስምምነትን በመሰረቱ ማሳደግ፣ ሴቶችን በሰላም ግንባታ ጥረቶች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የማህበረሰቡን እና የመህረሰብ መሪዎችን የሰላም ጠበቃነት ሚናቸውን መጠቀም፣ ሴቶች በአካባቢ እና በአገር አቀፍ ደረጃ በሰላም ግንባታ ስራዎች እንዲሰማሩ እና መብቶቻቸው እንዲከበሩ ለማድረግ ስልጠና እና ድጋፍ መስጠት። በትጥቅ ትግል ግጭት ወይም ከዚያ አውድ ውጪ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የድጋፍ መረቦችን መዘርጋት (support networks) እና ደህንነታቸው የተጠበቀ ማገገሚያ ቦታዎችን ማመቻት፣ የምክር፣ የህግ ድጋፍ እና የኢኮኖሚ ድጋፍን በመስጠት ከመንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ሲቪክ ማህበራት ይጠበቃል።

## አለምአቀፍ አጋሮች

በኢትዮጵያ ሰላም ግንባታ እና ግጭት አፈታት ጅምር ላይ አለም አቀፍ አጋር አካላት የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ መስጠት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ለአካባቢው ላሉ የሰላም ተዋናዮች አቅም ግንባታ መርሃ-ግብሮችን መንደፍ፣ የውይይት ሂደቶችን ማመቻቸት እና ሁሉን አቀፍ የሰላም ግንባታ አቀራረቦችን በማስፋፋት ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። የሴቶችን የትምህርት፣ የጤና አጠባበቅ እና የኢኮኖሚ እድሎች ለማሻሻል፣ የደህንነት ችግሮችን እና የአመፅ መንስኤዎችን ለመፍታት ያለሙ መርሃ-ግብሮችን ለይቶ የገንዘብ ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል። የሀገር ውስጥ ተቋማትን ለማጠናከር እና ሴቶች በየደረጃው ሰላምና ደህንነትን በተመለከቱ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስራዎችን መደገፍ ይኖርባቸዋል ።

# ዋቢዎች/References


የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ (CSA) [ኢትዮጵያ] እና የዓለም ባንክ። 2018. የኢትዮጵያ ሶሺዮ ኢኮኖሚ ጥናት 2017/18. የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት. አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ (ሲኤስኤ) [ኢትዮጵያ] እና አይሲኤፍ። 2016 የኢትዮጵያ የስነ-ሕዝብ እና የጤና ዳሰሳ 2016 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ እና ሮክቪል፣ ሜሪላንድ፣ አሜሪካ፡ ሲኤስኤ እና አይሲኤፍ።

ክረስዌል፣ ጄ.ደብሊው እና ክረስዌል፣ ጄ.ዲ. (2017)። የምርምር ንድፍ፡ ጥራት ያለው፣ መጠናዊ እና የተቀላቀሉ ዘዴዎች አቀራረቦች። የሳጅ ህትመቶች.

የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት (ኢ.ኤስ.ኤስ.) [ኢትዮጵያ] 2021. የሠራተኛ እና የስደት ዳሰሳ ቁልፍ ግኝቶች. አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2019)፣ የቤጂንግ መግለጫ እና የድርጊት መድረክ (ቤጂንግ +25) አፈፃፀም ላይ የተደረገ አምስተኛው ሀገር አቀፍ ሪፖርት። ሰነድ https://shorturl.at/3JsU3 ላይ ይገኛል።

IFPRI (2012) የWEAI የመረጃ ማዕከል በhttp://weai.ifpri.info/ ይገኛል። ኦገስት 15፣ 2020 ላይ ተገኝቷል።


የዓለም ኢኮኖሚ መድረክ. (2019) የ2020 ዓለም አቀፍ የሥርዓተ-ፆታ ክፍተት ሪፖርት።




NETWORK OF ETHIOPIAN WOMEN'S ASSOCIATIONS


Tel: +251118217758
email: newaethiopia@gmail.com
www.newaethiopia.org

of.newa
newa_ethiopia
@newaethiopia
www.linkedin.com/in/newa




# የኢትዮጵያ ሴቶች ሁኔታና ፍላጎቶቻቸውን
## ለመለየት የተካሄደ ጥናት

**አጭር ሪፖርት**

የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Women and Social Affairs

Funded by
the European Union

NEWA

OXFAM